# እግዚአብሔር ያመልክትህ ክርስቶስ ያሳይህ

በአቶ አሰፋ ጃቴ

ሚያዝያ 1997 ዓ.ም.
(2005)

# የመጀመሪያው የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ጥናት

ጸሐፊና አሳታሚ:- አሰፋ ጃቴ
እርማት:- ዘነበ ገብረሐና

1ኛ እትም ሚያዝያ 1997 ዓ.ም
የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው::
ስለ መጽሐፉ አስተያየት ቢኖርዎት
በመ.ሣ.ቁጥር 16252፣
አዲስ አበባ ይጻፉልን::

# ማውጫ

ገጽ

## ክፍል አንድ


ሀ) የተገለጠ ሕይወት 1:1-4 .................................. 13

ለ) የብርሃን ሕይወት፣ 1:5-2:2 .................................. 18

ሐ) እውነተኛ ሕይወት፣ 2:3-11 .................................. 30

መ) የተትረፈረፈ ሕይወት፣ 2:12-17 .................................. 34

ሠ) የሐሰት ሕይወት፣ 2:18-27 .................................. 42

ረ) የወደፊት መጪ ሕይወት፣ 2:28 - 3:3 .................................. 48

ሰ) አሸናፊው ሕይወት፣ 3:4-10 .................................. 51

ሸ) የፍቅር ሕይወት፣ 3:11-24 .................................. 54


## ክፍል ሁለት


ሀ) የማወቅና የመለየት ሕይወት፣ 4:1-6 .................................. 57

ለ) እውነተኛ ሕይወት እንጻለ በፍቅር ይታወቃል፣ 4:7-21 .................................. 60

ሐ) አሸናፊና ሕያው የሆነ የክርስቲያን ሕይወት ፣ 5:1-12 .................................. 64

መ) የዘላለም ሕይወት ዋስትና፣ 5:13-21 .................................. 71

# እግዚአብሔር ያመልክትህ
# ክርስቶስ ያሳይህ

ክርስቶስ ብቻ የዓለም መድኃኒት ነው፤ የሐዋ. ሥራ 4:4-12

1. ክርስቶስ የሕይወት ውኃ እንደሆነ
   ዮሐ. 4:13,14፤ ዮሐ. 7:37-39 ተመልከት::
2. ክርስቶስ የዓለም ብርሃን እንደሆነ፣ ዮሐ. 8:12::
3. ክርስቶስ የሕይወት እንጀራ እንደሆነ፣ ዮሐ. 6:35
4. ክርስቶስ የሕይወት መንገድ እንደሆነ፣ ዮሐ. 14:5
5. ክርስቶስ ብቻ እውነት እንደሆነ፣ ዮሐ. 14:6
6. ክርስቶስ ብቻ ሕይወት እንደሆነ፣ ዮሐ.14:6
7. ክርስቶስ የሕይወት በር እንደሆነ፣ ዮሐ.10:9
8. ክርስቶስ ብቻ ከሰማይ በታች ለሰው የተሰጠ የመዳኛ መንገድ እንደሆነ፣ የሐዋ. ሥራ 4:12
9. ክርስቶስ ብቻ መልካም እረኛ እንደሆነ፣ ዮሐ. 10:11
10. ክርስቶስ ብቻ ሰላም ሰጭ እንደሆነ፣ ዮሐ. 14:27
11. ክርስቶስ ብቻ አማላጅ እንደሆነ፣ ሮሜ 8:34፤ 1ኛ ዮሐ. 2:12፤ 1ኛ ጢሞ. 2:3-6 ተመልከት
12. ክርስቶስ ፍቅር እንደሆነ፣ ዮሐ. 15:9-13
13. ክርስቶስ ፈራጅ እንደሆነ፣ ዮሐ. 5:23-27
14. ክርስቶስ ጌታና አምላክ እንደሆነ፣ ዮሐ. 20:28፤ ኢሳ. 9:6
15. ክርስቶስ እግዚአብሔር እንደሆነ፣ ዮሐ. 10:30
16. ክርስቶስ ብቻ ነው አርነት የሚያወጣ፣ ዮሐ. 8:32-36
17. ክርስቶስ የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ነው፣ ራእይ 19:16
18. ክርስቶስ ብቻ አልፋና ኦሜጋ፣ ፊተኛና ኋለኛ ነው፣ ራእይ 1:8

# የመጽሐፉ ዋና ዋና ክፍሎች

መጽሐፉ በሁለት ትልልቅ ክፍሎች ይከፈላል:-

1. ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 3 የእግዚአብሔር ልጆች በእርሱ ፊት እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ያብራራል፤
2. ከምዕ. 4 እስከ ምዕ. 5 የእግዚአብሔር ልጆች በዓለም ፊት እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ያስረዳል::

# በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ቃላት

1. ሕይወት
2. ብርሃን
3. ፍቅር ናቸው::

«ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም አንዳች እንኳ ያለ እርሱ አልሆነም:: በእርሱ ሕይወት ነበረች፤ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች፤» ዮሐ. 1:3-4::

«ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን፤» ሮሜ 11:36::

# መቅድም

## የመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት መጽሐፍ ጥናት እንዴት እንደ ተጀመረ::

በ1961 ዓ.ም. ከአምቦ ከተማ የኤስ አይ ኤም የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ ወደ ነበረበት በጅማ ከተማ ውስጥ ወደሚገኘው ወደ ጅሬን ቀበሌ ለትምህርት ሄጄ ነበረ:: በዚያ ትምህርት ቤት የሦስት ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ኮርስ ወስጄአለሁ::

ትምህርቴን በምጨርስበት በሦስተኛ ዓመት በ1963 ዓ.ም. የወንጌል አገልግሎቴን በጅሬን ከተማ፣ በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ ባለው ጸሎት ቤት በየሳምንቱ አገልግሎት እንድሰጥ ስለተጠየቅሁ በዚያች ቤተ ክርስቲያን በየሳምንቱ መስበክ ጀመርኩ:: በየሳምንቱ መልእክቶችን ሳዘጋጅ እግዚአብሔር ወደ ልቤ ያመጣው መልእክት የመጀመሪያውን የዮሐንስ መልእክት መጽሐፍ ጥናት እንድወስድና ለቤተ ክርስቲያኑ ምእመናን መልእክት እንዳስተምር ነበረ:: በዚህ ሁኔታ የመጀመሪያውን የዮሐንስ መልእክት ጥናት በዚያው ስፍራ ጀምሬ ሙሉ በሙሉ አስተምሬ ስለ ጨረስኩ እግዚአብሔር ለእኔም ሆነ ለዚያች ቤተ ክርስቲያን በዚህ መጽሐፍ በኩል ብዙ በረከት አፍስሶአል:: ስለዚህ የመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት ዛሬም ሕያውና የሚባርክ ስለሆነ፣ ለዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን ምእመንና ለሚያነቡት ሁሉ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ፣ ወደ ኅትመት እንዲመጣ ጥረት አድርጌአለሁ:: አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ጌታ ክብርና ምስጋና ይሁን፤ አሜን!

አሰፋ ጃቴ

# መግቢያ

## የመጀመሪያው የዮሐንስ መልእክት ደራሲው ማን ነው?

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ደራሲ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ሁሉ፣ የዮሐንስ መልእክትም የመጽሐፍ ቅዱስ አንዱ ክፍል ነው:: ስለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ተጽፈዋል፣ 1ኛ ጴጥ. 1:20-21:: እንዲሁም 2ኛ ጢሞ. 3:16 ይመልከቱ::

2. በስው በኩል ደግሞ ጸሐፊ የነበረው የእግዚአብሔር ባሪያ ሐዋርያው ዮሐንስ ነበረ:: ይህ ዮሐንስ የዘብዴዎስ ልጅ የያዕቆብ ወንድም ነበረ:: ሁለቱም ዓሣ አጥማጆች ነበሩ፤ ማር. 1:19-20::

   ሐዋርያው ዮሐንስ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር ወይም ተማሪ ነበረ:: ኢየሱስም ሐዋርያ ብሎ ሰይሞታል:: ዮሐንስ ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ይልቅ ለኢየሱስ የቅርብ ደቀ መዝሙር እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጽልናል፤ ዮሐ.13:23-25:: ኢየሱስ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ ያለውን በዮሐንስ ወንጌል 19:26-27 ይመልከቱ::

3. ሐዋርያው ዮሐንስ ለኢየሱስ የቅርብ ደቀ መዝሙር ስለ ነበረ ስለጌታ የዓይን ምስክር መሆኑን ገልጾአል፤ 1ኛ ዮሐ. 1:1-4 ይመልከቱ::

## መጽሐፉ መቼ ተጻፈ?

ጊዜው በእርግጥ ባይታወቅም ከ85-95 ዓ.ም. ገደማ በትንሹ እስያ በኤፌሶን ከተማ እንደ ተጻፈ ይገመታል::

## ለማን ተጻፈ?

በክርስቶስ ወንጌል ለሚያምኑት ምእመናን ሁሉ ነው::

## የመጽሐፉ ዓላማ ምንድን ነው?

1. የመጽሐፉ ዓላማ የሐሰት ትምህርቶችን መቃወምና ማጋለጥ ነው::

2. ዛሬም በዘመናችን እንደምናየው የሰይጣን የማታለያ ልዩ ልዩ የስሕተት ትምህርቶች ስላሉ፣ በመታለል ከጌታ እንዳንወሰድ ለቤተ ክርስቲያን ማስጠንቀቂያ እንዲሆን ነው፣ ዕብ. 2:1፣ ገላ. 1:6-9::

3. የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ አማኞች ደኅንነታቸውን አረጋግጠው እንዲያውቁና በእምነት ጸንተው ጠላት ዲያብሎስን እንዲዋጉትና እስከ መጨረሻ እንዲቆሙ ለማበረታታት ነው::

4. በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ጥብቅ የሆነ ግንኙነትና ኅብረት እንዲያደርጉ ያስተምራል::

# በዘመኑ የነበረ የሐሰት ትምህርት እንዴት ነበረ?

1. በየዘመናቱ ሐሰትን የሚዘራ ጠላት ዲያብሎስ ሥራውን አላቋረጠም፤ ማቴ. 13:24-30 ተመልከት:: የእርሱ መጨረሻው ግን እንዲህ ይሆናል አለ ኢየሱስ፣ ማቴ. 13:36-43 አንብብ:: ዲያብሎስ ሐሰተኛ ነው:: የሐሰትም አባት ነው:: ሐሰት ሲናገር ከራሱ ይናገራል፣ ዮሐ. 8:44:: ኢየሱስ፣ እርሱ ነፍሰ ገዳይ ነው ብሎአል::

2. በጌታችን የሐዋርያት ዘመንም ኖስቲስት የተባሉ ረቂቅ የስሕተት ትምህርት አስተማሪዎች ተነሥተው ነበር::

   <u>ዋና ትምህርታቸውም</u>:- የእግዚአብሔር ልጅ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር መምጣቱን የሚቃወም የጠላት መሣሪያ ነበረ:: ወንጌል ግን ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ስለ መምጣቱ ብዙ ይናገራል፣ ዮሐ. 1:14፤ ሉቃስ 1:35፣ ማቴ. 1:21-23፣ ፊልጵ. 2:5-11::

## የኖስቲስቶች ትምህርታቸው

1. ሥጋ ሁሉ ርኩስ ነው:: ሥጋ የሆነው አካል የሚጨበጥ ስለሆነ ርኩስ ነው:: ሙሉ ለሙሉ መንፈስ ከሆነው እግዚአብሔር ጋር ይፃረራል ይላሉ:: የሥጋ አካል ርኩስ ነው ሲሉ፣ ዘፍጥረት 1:31ን ይቃወማሉ ማለት ነው::

እግዚአብሔር በፍጥረት ሥጋንም ከፈጠረ በኋላ አየ፤ ሁሉ መልካም ነበረ ይላል። 1ኛ ጢሞ. 4:4-5።

2. መንፈስ ሁሉ ቅዱስ ነው። ቅዱስ መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር እንዴት ርኩስ የሆነ ሥጋ መልበስ ይችላል? የሚል ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን መንፈስ ሁሉ ቅዱስ አይደለም ርኩስ መንፈስም አለ ይላል፣ ማር. 5:8-13። መንፈስን ሁሉ አትመኑ ይላል፣ 1ኛ ዮሐ. 4:1-2። የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው ይላል። ስለዚህ የዘመኑ ስሕተት ትምህርት ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ መምጣቱንና በሥጋ ሞቶ ኃጢአታችንን በመስቀል ላይ እንደ ተሸከመ በእርሱ ቁስል እኛ እንደ ተፈወስን ይክዳል፣ 1ኛ ጴጥ. 2:24፤ ኢሳ 53:3-12።

3. በዘመናችንም ብዙ የእግዚአብሔርን ቃል የሚፃረሩ ትምህርቶች እንዳሉ በዚህ መልእክት ታገኛላችሁ።

አሰፋ ጃቴ

# ማሳሰቢያ፣

ይህ የመጀመሪያይቱ ዮሐንስ መልእክት ጥናት

1. መጽሐፉን በግል ለሚያጠኑ
2. ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች እንደሚረዳ ተስፋ አደርጋለሁ።
3. ይህ መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በየምዕራፉና በየቁጥሮቹ አብሮ ካልተነበበ ብዙም አይጠቅምም።

አሰፋ ጃቴ

# የመጀመሪያይቱ የሐዋርያው የዮሐንስ መልእክት ትርጉም ወይም ጥናት

## ዮሐንስ ማለት:-

በአይሁዶች ቋንቋ ትርጉሙ የእግዚአብሔር ስጦታ ማለት ሲሆን፣ በአማርኛ ደስታ ወይም ተድላ ማለት ነው፣ ሉቃስ 1:14::

## ሐዋርያ ማለት

1. በኢየሱስ ክርስቶስ አፍ ለሐዋርያነት ቦታ የተመረጠና የተጠራ ልዩ ጥሪ ያገኘ ማለት ነው::
2. ኢየሱስ ክርስቶስን በዓይኑ ያየ፣ በእጁ የዳሰሰ፣ የንግግሩን ቃል ከአፉ የሰማና የዓይን ምስክር የሆነ ሰው ነው፣ 1ኛ ዮሐ. 1:1፣ 1ኛ ቆሮ. 9:1፤ 15:8 ይመልከቱ::
3. ወንጌልን ለአሕዛብ ሁሉ ያደርስ ዘንድ በጌታ የተመረጠ ሰው ነው፣ ሐዋ.ሥራ 9:15፤ 22:14-16፤ 26:16-18 ይመልከቱ::

# ክፍል አንድ

ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 3 ድረስ የእግዚአብሔር ልጆች በእርሱ ፊት እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ያሳያል።

## ሀ) የተገለጠ ሕይወት፣ 1ኛ ዮሐ. 1:1-4 አንብብ

<u>ስለ ሕይወት ቃል</u> ቁ. 1፣2፤ የሕይወት ቃል የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ዮሐንስ ወንጌል 1:1-5። ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰው ልጅ ጠፍቶ የነበረውን ሕይወት ይዞ መጣ፤ ዮሐ. 10:10፤ ዮሐ. 5:39-40። ሕይወት ማለት ሕያው ሆኖ መኖር ነው። ለዘላለም መኖር ማለት ነው። በክርስቶስ ያመነ፣ ክርስቶስን የተቀበለ (ዮሐ.1:2)። ከእግዚአብ ሔር ጋር የአባትነትና የልጅነት ግንኙነት አግኝቶአል። የልጅነትም ሥልጣን ይቀበላል። በክርስቶስ ያመነ አዲስ ሕይወት አግኝቶአል። የዘላለም ሕይወት አግኝቶአል።

በክርስቶስ ያላመነ ሰው ሥጋዊ ሕይወት ብቻ ይኖረዋል፤ መንፈሳዊ ሕይወቱ ሞቶአል፤ ኤፌ. 2:1። አሁን በክርስቶስ ያላመነ ሰው የሚኖረው ሕይወት ኃጢአት ወደ ዓለም ወይም ወደ ሰው ሳይገባ በፊት የነበረ ዓይነት ሕይወት አይደለም። ሰው በኃጢአት ሳይወድቅ በፊት ሕያው የሆነ፣ ለዘላለም የሚኖር መንፈሳዊና ሥጋዊ ሕይወት ነበረው፤ ዘፍጥ. 2:7-8። እግዚአብሔርን የሚመስል ዓይነት፣ ለዘላለም የሚኖር ሕያው ሕይወት ነበረው። ዛሬ አንተም ሕያው የሆነ ሕይወት እንዲኖርህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ግን ያ ለዘላለም የሚኖር መንፈሳዊ ሕይወት ከሰው ተለየ፣ ጠፋ። እግዚአብሔርንም መምሰል ቀረ፣ የሰው ዘር ተረገመ፤ ዘፍጥ. 3:17። ከገነት ተባረረ፣ ዘፍጥ 3:22-24። መንፈሳዊ ሕይወት ከሰው ተለየ። ሰው በመንፈስ በሥጋ ተራቆተ፣ ዘፍጥ. 3:7-8። ከዚያ ቀጥሎ ሰው አንድ ዓይነት ሕይወት ብቻ ሆኖ ቀረ። ያውም ሥጋዊ ሕይወት ነው ወይም በደም ውስጥ የሚኖር ሕይወት ሆነ፤ ዘሌ. 17:11 አንብብ።

# የደም ሕይወት

በሰው ውስጥ ደም ባይኖር በሕይወት መኖር አይቻልም:: በሰውነታችን ውስጥ እስከ 5 ሊትር ደም ያህል አለ ተብሎ ይገመታል:: እንግዲህ የሰው ሕይወት ሞተርና ነዳጅ ደም ነው:: በልብ አመታት ምክንያት ደም በ23 ሰከንድ ጠቅላላ ሰውነትን አንድ ጊዜ ዞሮ ወደ ልብ ይመለሳል:: ልብ ወደ ሳምባ ደምን ሲገፋ፣ ሳምባ አየርን ቀላቅሎ እንደገና ወደ ልብ ይልካል:: ልብም እንደገና ወደ ሰውነት ይገፋዋል:: በዚህ ምክንያት ምድራዊ ሕይወታችን የሚኖረው በደም መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ሲገልጽ እውነት ነው:: ደም በመቶ ቀን (100) ውስጥ ይሞትና በአዲስ ይቀየራል:: ልብ ደምን ማሠራጨት ሲያቆም ወይም ከደም ጥቂት ሊትር ሲፈስ የሰው ሕይወት ያበቃል፣ ይሞታል:: ይህ ሕይወት የሚሞት ዓይነት ነው::

ስለዚህ ይህን አዲስ ሕይወት ይዞ የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

በዚህ መጽሐፍ በቁጥር 1 የሕይወት ቃል የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በአዳም ኃጢአት ምክንያት ጠፍቶ የነበረውን ሕይወት ይዞ መጣ:: ያ ሕይወት ሥጋ ለብሶ በሰው አደረ፣ ዮሐ. 1:14:: ሐዋርያው ዮሐንስ ያንን አዲስ ሕይወት ሊሰጠን የመጣውን ኢየሱስ ክርስቶስን በጆሮአችን ሰማን፣ በዓይናችንም አየን፤ በእጃችንም ዳሰስን፤ እርሱ ሕይወትን ይዞ የመጣ የዓለም መድኃኒት ነውና ተቀበሉ ይላል፣ ዮሐ.10:10:: እርሱን ለተቀበሉና ለሚያምኑ የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ እግዚአብሔር ሥልጣን ሰጣቸው ይላል ዮሐንስ 1:12:: አንተም ይህን እውነተኛ ሕይወት ለመቀበል በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን:: አዲስ ሕይወት እግዚአብሔርን የመምሰል ዓይነት ሕይወት በልብህ ውስጥ ይገባል:: አዲስ ሰው ትሆናለህ፣ 2ኛ ቆሮ. 5:17:

# የተገለጠ ሕይወት ግንኙነትን ያመጣል

ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ሊያገናኝህ መጣ:: ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቅህ መጥቶአል:: ከእግዚአብሔር

ጋር የሚያገናኝ እውነተኛ መንገድ እውነተኛ ሕይወት እርሱ ብቻ ነው፣ ዮሐ. 14:6:: ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቅህ መጥቶአልና ተቀበለው:: እርሱ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቅ የሚል መልእክት አለው፤ ሮሜ 5:10፣ 2ኛ ቆሮ. 5:18-21:: ከአምላክህ ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ መጀመሪያ ከጌታ ኢየሱስ ጋር መታረቅ አለብህ:: እርሱ የኃጢአትህን ብዛት በደሙ አጥቦ አንጽቶ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርብህ ይችላልና ፍቀድለት፣ ልብህን ስጠው፤ ምሳሌ 23:26:: ዮሐ. 1:12:: በእምነት ክርስቶስን ስትቀበል ወዲያውኑ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆን መብት ታገኛለህ፣ ዮሐ. 1:12፤ ሮሜ 10:9-10:: ከዚያ ቀን ጀምሮ እግዚአብሔር አባትህ፣ አንተም ልጁ መሆንህንና የአባትነትና የልጅነት ግንኙነት በመካከላችሁ ይፈጠራል:: ከዚያ ቀን ጀምሮ አባ አባት ብለህ የምትጠራበት መንፈስ በልብህ ውስጥ ይኖራል፤ ገላ. 4:4-6፤ ሮሜ 8:14-17:: እግዚአብሔር አባትህ አንተም ልጁ የመሆንህ ግንኙነት በእምነት ብቻ የሚገኝ ነው::

ስለዚህ አሁን እንዲህ ብለህ ጸልይ:: ቃል አውጥተህ ተናገር:: ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣ እኔ ኃጢአተኛ ነኝ፤ ማረኝ:: ከአሁን ጀምሬ በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምናለሁ፤ ኃጢአቴን ይቅር በል:: ከአሁን ጀምሮ ልጅህ አድርገኝ:: ስሜን በሕይወት መዝገብ ጻፍ: አንተ አባት ሁነኝ፤ እኔም ልጅህ ልሁን:: መንፈስህን በልቤ ላክ:: ሰይጣንን ክጄዋለሁ:: ክርስቶስን አምኜዋለሁ:: አሜን:: ይህን ጸልየህ ከሆነ የአባትነትና የልጅነት ግንኙነትህ ጀምሮአል ማለት ነው:: ደስ ይበልህ አመስግነው::

## የተገለጠ ሕይወት ኅብረትን ያመጣል፤ 1ኛ ዮሐ. 1:3-4

ኅብረት ማለት አንድነት ማለት ነው:: ስምምነት ማለት ነው፣ አሞጽ 3:3:: ሁለት ዓይነት ኅብረት አለ:: ይኸውም:-

1ኛ. ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት፣
2ኛ. ከሰዎች ጋር ኅብረት ነው::

## 1. ኅብረት ከእግዚአብሔር ጋር፣ ቁ. 3-6 አንብብ

ኅብረት ከእግዚአብሔር ጋር የሚመጣው፣

ሀ) የእግዚአብሔርን ጥሪ ስንቀበል ነው፣ ማቴ. 11:28፤ 1ኛ ቆሮ. 1:9

ለ) በልጁ በክርስቶስ ስም ስናምንና ሕይወት ስንጀምር ነው፣ 1ኛ ዮሐ. 5:12-13፣ ኤፌ. 2:8::

ሐ) የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሆነን በውስጣችን ለውጥ ሲጀምር፣ ሕዝ. 36:26::

መ) በእምነት በክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን በመንጻት ነው፣ ቁ.7

ሠ) እውነተኛ ደስታ ወደ ልባችን ሲመጣ ነው፣1ኛ ዮሐ.1:4፤ ዮሐ.15:11:: እውነተኛ ሰላም በልባችን ሲፈስ ነው፤ ዮሐ.14:27::

ረ) ወደ እርሱ ስንጸልይና ቃሉን ስናነብ፣ ዮሐ. 15:7፤ ማቴ. 7:7-11፤ ኤር. 29:12-13::

ሰ) በረከትን ያመጣል፣ ሉቃስ 11:26፤ ኤፌ. 1:3::

ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ቢፈልግ መንገዱ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው:: እርሱም ዓለምን ከእግዚአብሔር ጋር አስታርቆ አልና፣ 2ኛ ቆሮ. 5:19:: ስለዚህ ሰው በእምነት የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆን ይችላል:: በእምነት የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ትሆናለህ:: አዲስ ፍጥረት ትሆናለህ፤ 2ኛ ቆሮ. 5:17::

በክርስቶስ በማመን ካልሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነትና ኅብረት ሊኖር አይችልም:: በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ወደ እግዚአብሔር ኅብረት በሚገቡ እግዚአብሔር ይደሰትባቸዋል፤ ይወዳቸዋልም፣ ዕብ. 11:6::

## ኅብረት ከሰው ጋር ያመጣል፣ ቁ. 3-6

የተገለጠ ሕይወት ከሰው ሁሉ ጋር ኅብረትን ያመጣል፤ ዕብ. 12:14፤ ሮሜ 12:18፤ ገላ. 6:10::

1. በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያላመኑትን ሰዎች እንድንወድና እንድንጸልይላቸው ያደርጋል:: ስለ ጌታ እንድንመሰክርላቸውም ያደርጋል፤ ሐዋ. 1:8::

2. ከክርስቲያን ጋር ልዩ ኅብረትን ያመጣል፣ ቁ. 7ን አንብብ::

   ሀ) ፍቅርን ያመጣል፣ ዮሐ. 13:34-35፤ ዮሐ. 15:12:3
   ለ) በመተባበርና በመረዳዳት ሕይወት ውስጥ ያሳልፈናል፣ 1ኛ ተሰ. 5:15:: መለያየትና መከፋፈልን ያስወግዳል::
   ሐ) በሰላም እንድንኖር ያደርጋል፣1ኛ ተሰ. 5:13፤ ዮሐ.14:27፤
   መ) አንዱ ለሌላው የመጸለይ ኅብረት ውስጥ ያስገባል፣ ኤፌ. 6:18::

አንተስ ከሌሎች ጋር ኅብረት አለህ? ከሌሎች ጋር ኅብረትን ሊያመጣ የሚችል ከእግዚአብሔር የሚመጣ ኅብረት ነው:: እግዚአብሔርን የሚያውቁ ብቻ ናቸው እውነተኛ ኅብረትን የሚያውቁ::

- ከሰው ጋር ኅብረት የሚኖረን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሲኖረን ብቻ ነው::
- ከሰው ጋር ትክክል የምንሆነው ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል ስንሆን ብቻ ነው::
- ሰውን መውደድ የምንችለው እግዚአብሔርን ስንወድ ብቻ ነው::

ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ጀምር:: ከሰውም ጋር ኅብረት ይኖርሃል::

## የተገለጠ ሕይወት ደስታ እንዲፈጸም ያደርጋል፣ ቁ. 4

ደስታ ማለት ሕይወት ማለት ነው:: ሰው ለደስታ ሲል ብዙ ይለፋል፣ ይጥራል፣ ይሠራል፣ ይነግዳል፣ ይማራል፣ ይዝናናል፣ መኪናና ቤት ይገዛል፣ ያገባል:: ደግሞም ገንዘብ ካገኘ በኋላ በብዙ ደስተኛ የሚሆን ይመስለዋል::

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚገልጽልን ደስታ በሀብት ብዛት የሚመጣ አይደለም:: መክብብ 5:11 ሀብት ቢበዛ ደስታ ሳይሆን

በላተኛ ይበዛል ይላል:: እውነተኛ ደስታ በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው ሊመጣ የሚችል:: ልብን ሞልቶ አእምሮን የሚያልፍ ደስታ ወይም ሰላም በክርስቶስ ስም በማመን ብቻ ይመጣል፣ ፊልጵ. 4:7:: እውነተኛ ደስታ ከመንፈስ ቅዱስ ብቻ ወደ ልባችን ይፈስሳል፣ ገላ. 5:22:: እውነተኛ ደስታ ከእግዚአብሔር አዲስ ልብ ስናገኝ ብቻ ነው ወደ እኛ የሚደርሰው፣ ሕዝ. 36:26-28:: ከዚያም ደስታ ከልባችን ይፈልቃል እንጂ በገንዘብ ብዛትና በሌላ አይመጣም:: እውነተኛ ደስታ ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ኅብረት ሲኖረን ይመጣል:: እጅግም ይበዛል፣ 1ኛ ዮሐ. 1:4፣ ዮሐ. 15:11::

## የተገለጠ ሕይወት ብርሃንንና ጨለማን ለይቶ ያሳያል::

ቁ. 5 እግዚአብሔር ብርሃን ነው፤ ጨለማ በእርሱ ዘንድ የለም:: ጨለማ የሰይጣን ነው:: ብርሃንን ስናይ ያስደስተናል:: የውጭ ብርሃን እንዳለ፣ የውስጥ የልብ ብርሃንም አለ:: ብርሃን ደስ ያሰኛል:: ጨለማ ግን ያስፈራል፣ ያስጠላል:: ብርሃንና ጨለማ ሁለት ተቃራኒ ነገሮች ናቸው:: እግዚአብሔር የሚሰጠን ነገር ሁሉ ለጥቅም ነው:: ብርሃንም ለጥቅም ነው የተሰጠን:: እግዚአብሔር ብርሃን የሰጠበት ምክንያት እንዲያበራ ነው::

- ፍጥረታዊ ብርሃን (ፀሐይ) የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ብርሃን እንዲያይ ነው::
- ፍጥረታዊ ብርሃን የተፈጠረው ፍጥረት በሕይወት እንዲኖር ነበረ:: ብርሃን ጠቃሚ ነው:: ስለ ብርሃን ቀጥሎ ባሉት ቁጥሮች ውስጥ እንመለከታለን::

አንባቢ ሆይ፣ ላንተስ እውነተኛ ሕይወት ተገልጦልሃል?

## ለ) የብርሃን ሕይወት፣ 1:5 - 2:2 አንብብ

እግዚአብሔር ብርሃን ነው:: ለሕያዋን ፍጥረታት ሁሉ ውጫዊ ብርሃን እንደሚያስፈልጋቸው፣ እንዲሁ ለሰው ልጆች ውስጣዊ ሕይወት የእግዚአብሔር ብርሃን ያስፈልጋቸዋል:: ለውስጣዊ ሕይወት ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፣ ዮሐ.

8:12:: ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመጣ ሁሉ በጨለማ አይመላለስም:: የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ::

የልብ ጨለማ፣ ውስጣዊ የልብ ጨለማ የኃጢአት ውጤት ነው:: ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ስለማይቀበል በጨለማ ይኖራል፣ 1ኛ ዮሐ. 2:11:: እግዚአብሔር ግን ሰዎች ሁሉ ወደ ብርሃን እንዲመጡ አዝዞአል፣ 2ኛ ቆሮ. 4:6፤ ዘፍጥ. 1:3::

ቁጥር 5ን አንብብ:: በዓለም ያለው መከራ በሞላ ከልብ፣ ከውስጥ ጨለማ የመጣ የኃጢአት ውጤት ነው:: ሰው ግን ለኃጢአቱ ሳይጨነቅ ለውጤቶች ይጨነቃል:: መጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ስለሚል (ሮሜ 6:23)፣ ሰው የኃጢአት ውጤትን እያጨደ ነው:: እግዚአብሔር ብርሃን ነው:: ወደ እርሱ ስንመለስ ብቻ ነው የሕይወት ብርሃን የሚሆነውና ጨለማው የሚወገደው::

## ሦስት ዓይነት ጨለማ አለ

1. ተፈጥሮአዊ ጨለማ፤ ይህም እግዚአብሔር የፈጠረው የሌሊት ጨለማ ማለት ነው፣ ዘፍጥ. 1:2-3:: እግዚአብሔር ለዚህ ዓይነት ጨለማ መፍትሔ ሰጥቷል:: ያውም ብርሃንን በቀን እንዲሠለጥን፣ ፀሐይንና ከዋክብትን በማድረግ ብርሃን ሰጠ፤ ጨለማን አስወገደ::
2. የሞራል ጨለማ፤ ይህ ማለት ሌሎችን መጉዳትና ለራስ ስግብግብ መሆን፣ ራእይ 21:8፤ 1ኛ ቆሮ.6:9-10 ተመልከት:: ይህ ጨለማ በሰው ሕይወት የሞላ ሲሆን፣ የጥላቻ ፣ የጥል፣ የቂምና ግድያ የመሳሰሉት ናቸው:: ለዚህ ዓይነት ጨለማ እግዚአብሔር ራሱ ማስወገጃ አዘጋጅቶአል:: መፍትሔውና መድኃኒቱ ክርስቶስ ነው:: እግዚአብሔር ክርስቶስን አዘጋጅቶአል:: ይህ ዓይነት ጨለማ ክርስቶስን ስናምን ይወገዳል:: ለሞራል ጨለማ እግዚአብሔር ከኃጢአት ንጹሕ የሆነውን ልጁን ላከ:: ልጁም ራሱን አዋርዶ ሰው ሆኖ ከሰው ተወለደና ይህን ጨለማ ለማስወገድ በእኛ ፈንታ በመስቀል ላይ ሞተልን፣ ማቴ. 1:21:: የሰው የሞራል ጨለማ ይህን

ይመስላል፤ ሮሜ 1:28-31 ተመልከት:: የሞራል ጨለማ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ይወገዳል::

3. <u>የኅብረት ጨለማ:-</u> ይህ ዓይነት ጨለማ በክርስቶስ በሚያምኑት ክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ተደብቆ የሚኖር ኃጢአት ነው:: ይህ ዓይነት ጨለማ ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ያለውን ኅብረት የሚያበላሽ ነው:: ክርስቲያን ቶሎ ንስሐ ካልገባ ቀስ በቀስ ወደ ሞት ይመራዋል:: ይህ የኃጢአት ጨለማ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ኅብረት ያበላሻል:: ከሌሎች ክርስቲያኖች ጋር ያለውን ኅብረትም ያበላሽና በጨለማ እንዲሄዱ ያደርጋል:: ቶሎ ብሎ ከሌሎች ጋር እርቅ ካላደረገና ካላስተካከለ አደገኛ ነው:: እንዲህ ዓይነት ኃጢአት ክርስቲያን በጨለማ እንዲኖር ያደርጋል

ወደ ኅብረት ብርሃን የሚያመጣ 3 የብርሃን መንገድ አለ

1. <u>የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ</u>፤ መዝሙር 119:105 ሕግህ ለእግሬ መብራት ነው ይላል:: የእግዚአብሔርን ቃል በየቀኑ ብናነብብ ጨለማ ይወገዳል::
2. <u>የሕይወት ብርሃን</u>፤ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በምናምንበት ጊዜ የምናገኘው የውስጥ ብርሃን አለ:: እርሱ ወደ ሕይወት ኅብረት ብርሃን ያመጣል:: ጨለማውንም ያስወግደዋል፣ 2ኛ ቆሮ. 4:6::
3. <u>የኅብረት ብርሃን</u>፤ አንድ ክርስቲያን በየቀኑ በጸሎትና በንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘት የሚያደርገው ኅብረትና ከወንድሞቹ ጋር የሚያደርገው ኅብረት ጨለማን ያስወግዳል:: በእነዚህ በሦስቱ ኅብረቶች መመላለስ ባይችል ሦስት ዓይነት ጨለማ ይወድቅበታል ወይም ወድቆበታል ማለት ነው::

   1. የአእምሮ ጨለማ፣ ኤፌ. 4:18-19::
   2. የእግዚአብሔር ትንቢት፣ ራእይ ጨለማ፣ ኢዩ. 2:2፤ 1ኛ ሳሙ. 3:1::

3. እውነትን ማየት አለመቻል፣ የሰይጣን ጨለማ፣ ኤፌ. 6:12::

የኀብረት ጨለማ ከወደቀብን፣ ከጌታና ከሌሎች ጋር ሰላም አይኖረንም::

## <u>በጨለማ መመላለስ፣ ቁጥር 6 አንብብ</u>

በጨለማ መመላለስ ማለት ምን ማለት ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ አብዛኛውን ጊዜ ጨለማ ሲል:-

1. ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ መሄድ ማለቱ ነው፣ 1ኛ ዮሐ. 2:4:: ይህም እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል አድርግ የሚለውን አለማድረግ ወይም አታድርግ የሚለውን ማድረግ ነው::
2. ከእግዚአብሔር መንገድ ውጭ መሄድ ማለቱ ነው፣ ዮሐ. 14:6:: እውነተኛው መንገድ ክርስቶስ ነው:: ሰው ያለ ክርስቶስ እግዚአብሔር ይወደኛል ይል ይሆናል፤ ግን በእግዚአብሔር በኩል አይሆንም:: እንዲሁም ሰው ያለ ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመግባት ተስፋ ያደርግ ይሆናል፣ ግን አይሆንም፤ አልተፈቀደም::
3. ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ መኖር ማለቱ ነው፤ 2ኛ ቆሮ. 6:16-17:: ለምሳሌ፣ የትዳር ጓደኛ ስትመርጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርግ፣ ኑር:: ከጨለማ ሥራ ጋር እየተጓዝህ የእግዚአብሔር ነኝ ብትል ውሸተኛ ትሆናለህ፤ 1ኛ ቆሮ. 10:31::

## በብርሃን መመላለስ ማለት ምን ማለት ነው?

(ቁ. 7 አንብብ)

በብርሃን መመላለስ ማለት በክርስቶስ በወንጌል ብርሃን ውስጥ መኖር ማለት ነው፣ ዮሐ. 15:7:: ክርስቶስ በራሱ ብርሃን በእኛ ውስጥ እንዲኖር መፍቀድ ነው:: ሕይወታችንን ለእርሱ ማስረከብ ማለት ነው:: ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር

የሚያደርገው ኅብረት ማለት ነው:: መጣላትን ትቶ መስማማት ነው፤ መዋደድና መረዳዳት ሲሆን፣ አንድ ልብ፣ አንድ መንፈስ፣ አንድ አባት እንዳላቸው መረዳት ነው:: በሥጋ ዝምድናና በወገን ልዩነት፣ በመልክና በሀብት ሳይሆን፣ በክርስቶስ ኅብረት እንዳላቸው ማወቅ ማለት ነው::

## የክርስቶስ ደም ኃጢአትን ሁሉ እንዴት ያነጻል?

(ቁ. 7 አንብብ)

መጽሐፍ ቅዱስ የደም መጽሐፍ ነው ቢባል ውሸት አይደለም:: በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 460 ጊዜ ስለ ደም ተጠቅሶአል:: በብሉይ ኪዳን 203 ጊዜ:: በአዲስ ኪዳን ወደ 257 ጊዜ ተጠቅሶአል:: ክርስቶስ ራሱ በምድር በነበረ ጊዜ ስለ ራሱ ደም 40 ጊዜ ተናግሮአል:: ደም ሰውን ያድናልን? መልሱ አዎን ነው:: የሰው ደም ዋጋ ያለው ነገር ነው::

ስለዚህ ነው የሰው ለጅ በሥልጣኔ በኩል ደምን በደም ባንክ የሚያኖረው:: የብዙ ሰው ሕይወት በደም ምክንያት ይኖራል:: የአንድ ሰው ደም ለሌላ ሰው ይሆናል ወይ? መልሱ አዎን ነው:: የአንድ ሰው ደም ዓይነት ከሌላ ሰው ደም ጋር ሊመሳሰል ይችላል:: እንዲሁም የአንድ ሰው ደም ለሌላው የማይሆን ዓይነትም አለ:: ለሁሉም ሰው ሊሰጥ የሚችል ዓይነት ደም አለ:: የራሱን ዓይነት ደም ብቻ የሚቀበልም ሰው አለ:: ይህን ሐኪሞች ብቻ በምርመራ ያደርጉታል:: የደም ዓይነቶች A.B.O.፤ A+B ይባላል:: የአንዱን ደም ሌላው በማግኘት በሕይወት መኖር ይቻላል:: ደም በማጣት የሚሞቱም አሉ::

የክርስቶስ ደም ግን በዚህ ዓይነት አይሠራም:: የክርስቶስ ደም በመስቀል ላይ ለእኛ ሲል መፍሰስ ነበረበት:: የክርስቶስ ደም ለዓለም ሕዝብ በሙሉ በመስቀል ላይ መፍሰስ ያስፈልገው ነበር፣ ዕብ. 9:22:: የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የክርስቶስ ደም ብቻ ነው፤ ዮሐ. 1:29:: የእንስሳት ደም በብሉይ ኪዳን ዘመን ያስተሰርያል:: ኃጢአትን ይደመስስ ነበረ፣ ዘሌ. 17:11:: ደም ካልፈሰሰ የኃጢአት ይቅርታ አይገኝም ነበረ:: የዓለም ሕዝብ ሁሉ እንዲድን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ደሙን ለማፍሰስ

ራሱን አሳልፎ ሰጠ፣ 1ኛ ጢሞ. 2:3-6፤ ዮሐ. 19:18-34:: የክርስቶስ ደም መፍሰስ አለበት:: የክርስቶስ ደም በመስቀል ላይ ሲፈስ እግዚአብሔር በልጁ ለማያምኑት ሁሉ ይቅርታ ሊሰጥ ቃል ኪዳን አድርጓአል::

ስለዚህ ክርስቶስ ለሁሉ ሰው፣ በዓለም ሁሉ ፣ በሁሉ ዘመን በቂ የሚሆን ደሙን በመስቀል አሳልፎ ሰጠ:: አንድ ጊዜ የፈሰሰው ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃል ቁ.7 አንብብ:: ከፊተኛው ኃጢአት፣ ከአሁን ኃጢአት፣ ከወደፊት ኃጢአት ሊያነፃ በቂ ነው፣ ዕብ. 9:28:: የክርስቶስ ደም ያድናል ያጸድቃል:: የክርስቶስ ኢየሱስ ደም ለሰው ልጅ ጽድቅና ቅድስና በቂ ነው:: የክርስቶስ ደም ኃጢአትን ያጠፋል::

የክርስቶስ ደም በመስቀል ላይ የፈሰሰበት ምክንያት በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ያለ ደም አይነፃምና ነው:: ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ከኃጢአትና ከዘላለም ፍርድ እንዲድን የክርስቶስ ደም መፍሰስ ያስፈልገው ነበረ፣ ዕብ. 10:29-31፤ ዘጸ. 12:13:: ሰውም በክርስቶስ ደም አምኖ ሊድን በእምነት መቀበል አለበት፤ ዮሐ.3:16-18:: የክርስቶስ ደም ለእኔ ፈሶልኛል ብሎ በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ማመን አለበት:: በዚያን ጊዜ ይድናል፣ የሐዋ. 16:31::

## <u>ስለ ውሸትና ስለ መናዘዝ፤ ቁጥር 8-10 አንብብ</u>

በእነዚህ ቁጥሮች ሁለት ታላላቅ ነገሮች እንመለከታለን፣

1ኛ <u>ስለ ውሸት ነው</u>:: ቁጥር 6፣8 እና 10 ላይ ስለ ሦስት ዓይነት ውሸቶች ይናገራል::

1. በቁ. 6 ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት አለኝ ብዬ በኃጢአት ውስጥ የምኖር ከሆንኩ እዋሻለሁ ማለት ነው:: ሰው ተግባሬን ስለሚያይ ውሸታም መሆኔን ያውቃል ማለት ነው:: ውሸታም ከሆንኩ የሰይጣን ልጅ ነኝ ማለት ነው:: ሰይጣን የውሸት አባት ነውና፣ ዮሐ. 8:44 ተመልከት::
2. በቁጥር 8 ኃጢአት የለብኝም እያልኩ እውነትን ከተውኩኝ ራሴን በማታለል ራሴን ውሸተኛ አደርጋለሁ ወይም ራሴን

አታለልኩኝ ማለት ነው:: ሐዋርያው ዮሐንስ በነበረበት ዘመን የነበሩት የስሕተት አስተማሪዎች ኃጢአት እያደረጉ ኃጢአት የለብንም ይሉ ነበር:: ሰው ራሱን ተመልሶ ማየት ቢችል ኖሮ እንዴት መልካም ነበር::

ታሪክና ምሳሌ በተባለው መጽሐፍ ዝንጀሮ የራሷን መልክና ሁኔታ በመስተዋት ተመልክታ ምን ዓይነት አስቀያሚ ፍጥረት ነኝ ብላ ራሷን ጠላች ይላል:: ሰውም የሌላን ሰው ሁኔታ ማየት ትቶ የራሱን ሁኔታ ወይም ኃጢአት ቢመለከት እንዴት ጥሩ ነበር:: እኔ ጥሩ ሰው ነኝ በማለት ራሳችንን እናታልል:: ራሳችንን እያሞጋገስን እንኑር:: ከሁሉ በላይ የሆነውን እግዚአብሔርን ማታለል ግን አይቻልም::

አርቴፊሻል ወርቅ ይዞ ወርቅ ሠሪውን ማታለል አይቻልም:: የአሻንጉሊት ሰዓት (መጫወቻ) ይዞ ሰዓት ሠሪውን ማታለል አይቻልም:: እንዲሁም እግዚአብሔርን ማታለል አይቻልም:: እርሱ ሁሉን ያውቃል::

3. በቁጥር 10 ላይ ሰው ሆነን ኃጢአት የለብንም ብንል እግዚአብ ሔርን ውሸተኛ ነህ ማለታችን ነው:: በሮሜ 3:23 ላይ ሁሉ ኃጢአትን ሠርቶአል ብለህ የተናገርኸው ቃል ውሸት ነው ማለታችን ሲሆን፣ እግዚአብሔር አንተ ውሸታም ነህ፣ እኔ ግን ውሸት የለብኝም ማለታችን ነው:: ለምሳሌ እንዲህ ማለታችን ነው:- አንድ ቀን ውሸት ተናግሬ አላውቅም፣ ሰውን አምቼ አላውቅም፣ ሰውን ተሳድቤም አላውቅም፣ ተቆጥቼም አላውቅም፣ ወይም ሠርቄ ተሳስቼ አላውቅም፣ ወዘተ... ማለታችን ነው:: ይህንን በማለታችንና በማሰባችንም ኃጢአት ሠርተናል፣ ሮሜ 6:23:: ስለዚህ እኛ ሰዎች ውሸታሞች ስንሆን እግዚአብሔር ግን እውነተኛ ነው፣ ሮሜ 3:4::

2ኛ ኃጢአትን ስለ መናዘዝ፤ ቁ. 9 አንብብ

በኃጢአታችን ብንናዘዝ ይለናል:: ኃጢአትህን ተናዘዝ ማለት ነው:: ኃጢአትህን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግረህ ይቅርታ ጠይቀው:: ከአሁን ጀምሮ ኃጢአት ማድረግን ትቼ ወደ ቅዱስ አምላኬ ወደ አንተ ተመልሻለሁ በል ማለት ነው:: ይህን

ብታደርግ ምሕረት ታገኛለህ:: ኃጢአትህን ይቅር ሊል ከዐመፃም ሁሉ ሊያነጻህ የታመነና ጻድቅ ነው:: ምሕረት የምናገኘው የተናገረውን ቃል የማይሽር ጌታ ስላለ እንጂ ስለ እኛ መናዘዝ ብቻ አይደለም:: እንግዲህ በኃጢአት ምክንያት በሐፍረት የተሞላ ፊትህን ወደ ጌታ መልስ፤ ምሳሌ 28:13::

## ለማን እንናዘዝ?

በመጀመሪያ ቀጥታ ለክርስቶስ ነው::

1. ለአንተ አማላጅና ጠበቃ ነውና፣ ምዕ. 2:1፣ 1ኛ ጢሞ. 2:5::
2. አንተን የሚረዳ ወዳጅህ ነው፣ ዮሐ. 15:12-15::
3. ለአንተ ካህን ሆኖ ሊያስታርቅህ ሞቶአልና፣ ምዕ. 2:2

ስለዚህ ኃጢአትህን አትሸከም፣ ለክርስቶስ በመናዘዝ አስረክበው::

<u>ሁለተኛ</u> የበደልከውን ሰው ሄደህ ይቅርታ ጠይቅ፣ ማቴ. 5:23-25፤ 1ኛ ዮሐ. 4:20-21::

## ያልተናዘዙት ኃጢአት ምን ያደርጋል?

1. በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላላመኑት ሰዎች፤ ኃጢአት ወደ ገሃነመ እሳት ያደርሳቸዋል፣ ማቴ. 25:41::

2. በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመኑትን ሰዎች ያልተናዘዙት ኃጢአት ከእግዚአብሔር ኅብረት ይለያቸዋል:: ያልተናዘዝነው ኃጢአት እስከ ክርስቶስ ፍርድ ዙፋን ፊት ድረስ ስለሚቆይ ቶሎ ብለን በመናዘዝ ይቅርታ ማግኘት አለብን:: እኛ ኃጢአታችንን ስንናዘዝ ምሕረት መስጠትና ማንጻት የክርስቶስ ሥራ ነው:: በቃሉቹ ብንታመን በእርግጥ ከኃጢአት መንጻታችንን በእምነት እናውቃለን:: የእግዚአብሔር መንፈስ ለመንፈሳችን ይመሰክር ልናል፣ ሮሜ 8:16 ቁጥር 11 ተመልከት:: በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ምሕረት እናገኛለን፣ ኤፌ. 2:8::

## ከኃጢአት የምንነፃው በሁለት ዓይነት መንገድ ነው

1. በክርስቶስ ከማመናችን በፊት የሠራነው ኃጢአት በክርስቶስ ስም ስናምን ይነፃል።
2. በክርስቶስ ካመንን በኋላ ለሠራናቸው ኃጢአት ስንናዘዝ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው፤ ቁ. 9 ተመልከት።

<u>በእግዚአብሔርና በልጁ</u> በኢየሱስ ክርስቶስ መካከል አንድ ውል አለ። ያውም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በኃጢአተኞች ፈንታ ሞቶ የኃጢአታቸውን ዕዳ እንዲከፍልላቸው፣ ቆላ. 2፡11-15። እግዚአብሔ ርም ኃጢአታቸውን ለክርስቶስ ተናዝዘው በእርሱ ደም በእምነት ምሕረት ለሚፈልጉት ሁሉ ምሕረት እንዲያገኙ ያደርጋል፣ 2ኛ ቆሮ. 5፡19። በዚህ ውስጥ አንተም አለህበትና ኃጢአትህን ለክርስቶስ ተናዝዘህ አሁኑኑ ምሕረት ለመቀበል ትችላለህ።

# ምዕራፍ ሁለት

ልጆቼ ሆይ፣ ኃጢአት እንዳታደርጉ፤ 2፡1-2 አንብብ።

በዚህ መጽሐፍ ብቻ ልጆቼ የሚለው ቃል 6 ጊዜ ተጽፎ ይገኛል። እግዚአብሔር ማንንም ልጆቼ አይልም፤ የራሱን ልጆች ብቻ እንጂ። ለእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ከእርሱ መወለድ አለብን። የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን የምንወለድባቸው ሦስት መንገዶች አሉ። ሦስቱም ወደ እግዚአብሔር ልጅነት ያመጣሉ።

1ኛ. ክርስቶስን በእምነት መቀበልና ማመን ነው፣ ዮሐ. 1፡12።

2ኛ. በመንፈስ ቅዱስ ዳግመኛ መወለድ ነው፣ ዮሐ. 3፡3-5።

3ኛ. በቃሉ በወንጌል መወለድ ነው፣ ያዕቆብ 1፡18።

በእምነት ልጆቼ የሆኑት እነዚህ ከሰይጣን ቤተሰብነት ወጥተው እግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ይገባሉ። በእግዚአብሔር ልጅ ሥራ ስላመኑ የልጅነት መብት እንዲያገኙ ሥልጣን ተሰጣቸው፣ ዮሐ.1፡12። እግዚአብሔር አባት፣ እነርሱም ልጆች ሊሆኑ ቻሉ። ስለዚህ ነው ልጆች ተብለው ሊጠሩ የቻሉት፣ 1ኛ ዮሐ. 3፡1። ስለዚህ ኃጢአት እንዳታደርጉ ተባሉ፣ ቁ.1። አንተስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ?

## ኃጢአት ምን ያደርጋል?

ኃጢአት አባትንና ልጅን ያቀያይማል። እንደ አዳም ይለያያል፣ ኢሳ. 59፡2። የአባትንና የልጅን ኅብረት ያበላሻል። ፍርሃትንና ሐፍረትን በመካከላቸው ይፈጥራል።

ክርስቲያን ሁለት ዓይነት ሰውነት በውስጡ አለው። አንደኛው መንፈሳዊ ሰውነት ነው። ይህ የውስጥ ሰውነት ኃጢአትን ይጠላል። ሁለተኛው ሥጋዊ ሰውነት ነው። ይህ ሰውነት በውስጣችን የሚኖር ኃጢአትን ይወዳል፣ ሮሜ 7፡22-25፤ ገላ. 5፡16 ና 17 ተመልከት። በክርስቶስ ስናምን ያ ሥጋዊ ሰውነት ኃጢአትን የሚወድ ሰውነት ከእኛ ተገፍፎ አይወገድልንም። ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ደካማ ሆኖ

ይቀመጣል:: አንዳንዴም ብድግ ይልና መንፈሳዊ ሕይወትን ሊያሸንፍም ይሞክራል:: ሁለተኛው ዓይነት ሰውነት መንፈሳዊ ሕይወትን ይወዳል፣ ኃጢአትን አይወድም:: መንፈስ ቅዱስም ይህን ሰውነት ሊረዳ ይወዳል::

ምሳሌ፣ አንድ ጊዜ አንድ ሰው ወደ ወንጌል አገልጋይ መጥቶ ጥያቄ አቀረበ:: እንዲህም አለው፣ በሕይወቴ ውስጥ ሁለት ውሻዎች አሉ:: አንደኛው ጥቁር ሌላው ደግሞ ነጭ ነው:: ሁለቱም ሁልጊዜ ይጣላሉ:: እኔ ላሸንፍ እኔ ላሸንፍ ይላሉ:: ማን ያሸንፍ ይሆን ብሎ ጠየቀው:: ወንጌላዊውም አንተ የምትደግፈው ወይም የምትረዳው ውሻ እርሱ ያሸንፋል ብሎ መለሰለት ይባላል:: እንዲሁም አንተ ክርስቲያን ሆይ፣ ዛሬ በሕይወትህ ማንን ትደግፋለህ? ኃጢአትን ወይስ ጽድቅን? ስለዚህ አንተም ኃጢአት አታድርግ:: በኃጢአት ውስጥ ልትኖር አያስፈልግህም:: የኃጢአት ልማድ እንዳይኖርህ መልመድ ያስፈልጋል:: የኃጢአት ቀጠሮ ወስደህ ኃጢአት አታድርግ:: ለኃጢአታችን የሞተው ክርስቶስ የኃጢአታችንን ዕዳ ዋጋ ከፈለልን:: ኃጢአታችንን በመስቀል ገድሎአል፣ ኤፌ. 2:16::

እንዲሁም ደግሞ ክርስቶስ ከሞት ተነሥቶ ሕያው በመሆኑ፣ በሕይወቱ የኃጢአትን ኃይል አጠፋ:: ለእኛም የድል አድራጊነት ኃይልና ሥልጣን ሰጠን ማለት ነው፣ 1ኛ ቆሮ. 15:55-57፤ ሮሜ 8:37፣ ሮሜ 6:12-14:: ስለዚህ ክርስቲያን የኃጢአት ባሪያ መሆን የለበትም:: ክርስቲያን ኃጢአትን ሲሠራ ክፉ ልጅ አባቱን እንደሚያሳዝን ያህል እግዚአብሔርን ማሳዘኑ ነው::

ታዲያስ ክርስቲያን ኃጢአትን ሊከላከል ይችላል ወይ? መልሱ አዎን ነው:: ክፉ አሳብ በአንጐልህ ወይም በውስጥ በአሳብህ እንዳይመጣ ልትከላከል አትችል ይሆናል::

አንድ የወንጌል አገልጋይ እንዲህ አለ፣ አሞራ ካንተ በላይ በሰማይ በአየር ላይ እንዳይበር መከልከል አትችልም:: ነገር ግን በአንተ ራስ ላይ ጐጆ እንዳይሠራ መከልከል ትችላለህ:: ኃጢአትም በአሳባችን ሊመጣ ይችላል:: ግን ሄደን መፈጸም የለብንም:: ጌታ ስለ ለወጠን "ሁሉን በሚያስችለን በክርስቶስ

ኢየሱስ ኃይል ኃጢአትን እምቢ ማለት" እንችላለን ማለት ነው፤ ፊልጵ. 4:13።

በድንገት በኃጢአት ብትወድቁ እንኳ በአብ ዘንድ ጠበቃ ወይም አማላጅ አለ። እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ቁ. 2።

ለክርስቲያን የሚረዱ ሁለት ጠበቃዎች አሉ። እነርሱም፦

1. መንፈስ ቅዱስ ነው፣ ሮሜ 8:26-27። በምድር ኑሮ የሚረዳ ድካምህን ስለሚያውቅ ያግዝሃል።
2. ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ ቁ. 1፣ ሮሜ 8:33-34፤ ዕብ. 7:25። እርሱ በሰማይ የሚቆምልህ ጠበቃ ነው።

ለነፍስህ ጠበቃ አለህ? ኢየሱስ ክርስቶስን ያዘው። ከእርሱ ሌላ ማንም የለምና፤ የሐዋ. 4:12፤ 1ኛ ጢሞ. 2:5-6። እውነተኛ ጠበቃ እርሱ ነው ፤ የክርስቲያን ጠበቃ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ የጥብቅና ሥራ ፈጽሞአል።

1. በእግዚአብሔር ፊት የአዳኝነቱን ሥራ ጨርሶአል። ስለዚህ አዳኝ እርሱ ነው። ከእርሱ ሌላ አዳኝ የለም።
2. በእግዚአብሔር ፊት የመሥዋዕትነቱን ሥራ ፈጽሞአል። ስለዚህ ካህን እርሱ ብቻ ነው፤ ዕብ. 4:14-16።
3. በእግዚአብሔር ፊት ከኃጢአት ሰዎችን መዋጀትና የጽድቅን ሥራ ሠርቶ ጨርሷል። ገና የሚሠራው ሥራ አለ።

## ገና የሚሠራቸው ሥራ

1. የጥብቅናና የአማላጅነትን ሥራ ገና አላቆመም፣ ዕብ. 9:28። አሁንም እየሠራ ነው።
2. ገና ክርስቲያኖችን የመቀደስ ሥራ እየሠራ ነው፣ 1ኛ ጴጥ.1:15-16።
3. ሕዝቡን የመጠበቁን ሥራ እየሠራ ነው፣ መዝ. 23:1-6።
4. ኢየሱስ ሰዎችን የመውደድ ሥራውን እንደ ቀጠለ ነው፣ ዮሐ. 5:9።

5. የፍርድ ሥራ አላለቀም፣ ዮሐ. 5:23 ና 27::

ሀ) የመኖሪያ ስፍራ አዘጋጅቶአል፤ ቢሆንም ገና አልተጠራንም፣ ዮሐ. 14:3::

ለ) በዙፋኑ ተቀምጠናል፤ ግን ገና አልተጠራንም፤ ኤፌ. 2:7::

ሐ) ስማችን በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎአል፣ ሆኖም ገና አልተጠራንም፣ ሉቃስ 10:20::

መ) ከፍርድ አምልጠናል፤ ዮሐ. 5:24፤ ገና በፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለን፣ ሮሜ 14:10:: ስለዚህ ጠበቃችን ሥራ እየሠራ ነው::

<u>ክርስቶስ ለኃጢአታችን ማስተሰሪያ ነው፤ ቁ. 2 አንብብ</u>

እርሱ ክርስቶስ ለዓለም ሁሉ ኃጢአት በቂ ማስተሰሪያ ነው:: በሞቱና በፈሰሰው ደሙ ለሚያምኑት ሁሉ የኃጢአትን ይቅርታ ይሰጣል:: ኃጢአትን ይደመስሳል::

ሐ) <u>እውነተኛ ሕይወት</u>፣ 1ኛ ዮሐ. 2:3-11 አንብብ

አሁን ባነበብነው ክፍል ውስጥ ትእዛዝ የሚለው ቃል 5 ጊዜ ያህል ተደጋግሞ ይገኛል::

<u>ትእዛዝ ማለት ምን ማለት ነው?</u>

መልሱ ሕግ ማለት ነው:: <u>የማን ሕግ?</u> መልሱ የእግዚአብሔር ሕግ ነው:: የእግዚአብሔር ሕግ ስንት ዓይነት ነው? መልሱ የእግዚአብሔር ሕግ አንድ ዓይነት ነው ሲሆን፣ አቋሙ ግን ሁለት ዓይነት ነው:: ይኸውም:-

1. የብሉይ ኪዳን ዘመን ሕግ ሲሆን፣ በሙሴ በኩል ለአይሁዶች የተሰጠ ሕግ ማለት ነው::
2. የአዲስ ኪዳን ሕግ ሲሆን፣ በክርስቶስ በኩል ለክርስቲያን የተሰጠ ሕግ ማለት ነው:: ሕግ ሁሉ የፍቅር መልእክት

አለው። እግዚአብሔር ለሰዎች ፍቅሩን የገለጸበት መንገድ ነው።

## የብሉይ ኪዳን ትእዛዝ ምን ዓይነት ነበረ? ዘፀ. 20

መልሱ:-1. በድንጋይ ላይ የተጻፈ ነበር፣ ዘፀ.31:18፤ 32:15-6።
2. የሚሰበር ዓይነት ነበር፣ ዘፀ. 32:19፤ በኋላ በሙሴ እጅ እንደገና ተጻፈ።
3. ጽሕፈት ነበር (ፊደል) ማለት ነው፣ ሮሜ 7:6፤ 2ኛ ቆሮ. 3:6።
4. ውጫዊ ነበር፣ ማቴ. 23:25-28።
5. የሚቀመጠውም በሳጥን ውስጥ ነበረ።

በተሰጣቸው 10 ሕገ ቃላት አሳዛኝ ነገር ሕጉ ንጹሕ ሲሆን፣ ሰው ግን በሕጉ ሊቆም አልቻለም። ሕግን መፈጸም አቃተው። ለምሳሌ ያህል፣

1ኛ/ ሕግ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ ይላል። እስራኤላውያን ግን ብዙ ጊዜ ሕጉን አፈረሱት። ገና እንደተሰጣቸው አጠፉ፣ ዘፀ. 32:1-10። አንዳንድ ጊዜ ሕጉን ለመጠበቅ ወይም ለመፈጸም ተስፋ ሰጡ፤ ኢያሱ 1:16-18። ግን ተመልሰው ተላለፉና አፈረሱት፤ መሳፍንት 2:11-13 ምዕ. 7:12 ተመልከቱ።

2ኛ/ ሌላው ደግሞ ሁለተኛ ያፈረሱት ሕግ አባትህንና እናትህን አክብር የሚለውን ሲሆን፣ ምን እንዳደረጉት በማቴዎስ 15:3-6 አንብቡና ኢየሱስ የተናገረውን አስተውሉ።

3ኛ/ አትግደል የተባለውን ሕግ ምን እንዳደረጉ በማቴዎስ 23:34-35 ተመልከቱ። በኢየሱስ አንደበት የተነገረ ስለሆነ ወደቁበት ሌላው ቀርቶ ክርስቶስንም ገድለዋል።

4ኛ/ አታመንዝር የተባለውን ሕግ በዘኁልቁ 25:1 ጀምሮ አንብቡ። አመነዘሩ። እንዲሁም ነቢያት ሁሉ ስለ እሥራኤውያን ዝሙት ሳይናገሩ አላለፉም፤ ኤርምያስ 25:4።

ለምን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አልፈጸሙም? ምክንያቱ ምን ነበረ?

1ኛ/ ሕጉ ከአቅማቸው በላይ ከባድ ሸክም ስለ ነበረ መሸከም አቃታቸው፣የሐዋ. 15:29::

2ኛ/ ኃይል አልነበራቸውም፣ 1ኛ ቆሮ. 15:56:: ሕጉ ኃይለኛ ስለነበረ አሸነፋቸው::

3ኛ/ ሕግ የሚገድል ሆነባቸው፣ ሮሜ 7:7-10::

4ኛ/ ሕግ ኃጢአትን የሚያሳይ እንጂ የሚያነፃ አልነበረም፤ ሮሜ 7:7:: ስለዚህ እግዚአብሔር እኔ አቋምን እለውጣለሁ አለ፣ ኤር. 31:31-34:: አዲስ አደርጋለሁ አለ::

## የአዲስ ኪዳን ሕግ ወይም ትእዛዝ

ሕዝቅኤል 36:26 አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ የሚል ነበረ:: የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ በተገለጠ ጊዜ በማቴዎስ 11:28-30 ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፣ እኔ አሳርፋችኋለሁ አለ:: ይህ ሸክም የሕግ ክብደትን ጭምር ያካተተ ነው:: ከዚህ ሸክም ክርስቶስ ሊያሳርፈን መጣ:: የክርስቶስ ሸክም ቀላል ነው፤ ቀንበሩም ልዝብ ነው::

ክርስቶስ የሕግ ሸክምን ራሱ ሊረዳ ይፈልጋል:: ሸክምን ሊያቃልልን መጣ:: የክርስቶስ ወንጌል በሥራና በልፋት ሳይሆን በእምነት ብቻ መዳን እንደምንችል ይገልጽልናል፣ ኤፌ. 2:8:: ስለዚህ የክርስቶስ ሸክም ከሕግ ሸክም ይልቅ ቀላል ነው:: አንተም በእምነት ጌታን ተቀብለህ መዳን ትችላለህ::

የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንደሚሉት የብሉይ ኪዳን 10 ትእዛዛት በሁለት ትልልቅ ክፍል ይከፈላሉ:: ከአንደኛው እስከ አምስተኛው ድረስ ያሉት ትእዛዛት እግዚአብሔርን ያማከሉ ሲሆኑ፣ ከስድስተኛው እስከ አሥረኛው ያሉት ደግሞ ሰውን ያማከሉ ናቸው:: አንተም በአሪት ዘፀአት ምዕራፍ 20 ያለውን አጥናና ተረዳ::

የብሉይ ኪዳን ሕግ በዋናነት የያዘው አታድርግ የሚለውን ሃሳብ ነው። ለምሳሌ፣ አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ ወዘተ...። አንድ ነገር አስታውስ፣ የብሉይ ኪዳንን ትእዛዛት በሙሉ ብትጠብቅ እንኳን ለእግዚአብሔር የምታቀርበው ምንም መልካም ነገር የለህም። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ "የሰው ልብ ተንኮለኛ ነው" ይላል ኤር. 17፡9። ስለዚህ እኛ መልካም ሥራ ሠርተን መዳን የማንችል ነን፣ ሮሜ 3፡11-20፤ ገላ. 2፡17,21፣ ምዕ. 3፡10።

የአዲስ ኪዳን ሕግ ግን አድርግ የሚል እንጂ አታድርግ የሚል አይደለም፤ ማቴ. 22፡38-40። ያውም የአዲስ ኪዳን ትእዛዛት ሁለት ብቻ ናቸው። እነርሱም፡-

<u>አንደኛው</u>፣ እግዚአብሔርን ውደደው የሚል ሲሆን፣ እርሱም አድርግ ወይም ክርስቶስን ተቀበል፣ እመን ትድናለህ የሚል ነው፣ ዮሐ.1፡12፣ የሐዋ.16፡31።

<u>ሁለተኛው</u>፣ ባልንጀራህን ውደደው የሚል ነው። ማለት ሰውን አፍቅር ወይም አድርግ እያለ ነው። ሕግ ሁሉ በዚህ በአንድ ቃል ይጠቃለላል። እርሱም ፍቅር ነው፤ ገላ. 5፡14። እግዚአብሔርን ውደድ እንዲሁም ሰውንም ውደድ የሚል ነው። የክርስቶስን ፍቅር ቅመስ ነው የሚለው።

የክርስቶስን ፍቅር መቅመስ ማለት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸም ማለት ነው፣ ዮሐ. 13፡34። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ወደደህ በእውነት ቢገባህ ትእዛዙን ትፈጽማለህ፣ ዮሐ. 15፡9-17።

በ1ኛ ዮሐንስ 2፡3 ላይ ፍቅሩን ብናውቅ ትእዛዙን እንጠብቃለን፤ ትእዛዙን እንደጠበቅን የምናውቀው በፍቅር ነው ይላል።

1ኛ ዮሐ. 2፡5 አንብብ። ፍቅር ካለህ ትእዛዙ በአንተ ዘንድ አለ። በአንተ ተፈጽሞአል። በክርስቶስ ፍቅር ትእዛዝን መጠበቅ በጣም ቀላል ነው።

ቁ. 6 ክርስቶስ በፍቅር እንደ ተመላለሰ፣ አንተም በፍቅር ተመላለስ። ሮሜ 13፡8-10፤ ቆላስ. 3፡14።

1ኛ ዮሐ. 2:7-11 አንብብ:: አሮጌው ትእዛዝ በአዲስ ትእዛዝ እንደ ተለወጠ 5 ነገሮችን ተመልከት::

1. አዲሱ ትእዛዝ እውነተኛነትን ይገልጻል::
2. አዲሱ ትእዛዝ ወደ እውነተኛ ብርሃን ያወጣል::
3. አዲሱ ትእዛዝ ወንድምን መውደድ ነው::
4. አዲሱ ትእዛዝ ፍቅር ማሰናከያ አይኖርበትም::
5. አዲሱ ትእዛዝ ጨለማ አይኖርበትም

ስለዚህ በአዲሱ ትእዛዝ ለመግባት የክርስቶስ ፍቅር በልብህ እንዲገባ ፍቀድ:: ጌታን በእምነት ተቀበል:: እውነተኛ የሆነ ብርሃን በሕይወትህ ይገለጻል:: ጨለማና ማሰናከያ ከሕይወትህ ይወገዳል፣ ዮሐ. 8:12::

## መ) <u>የተትረፈረፈ ሕይወት</u>፣ 1ኛ ዮሐ. 2:12-17 አንብብ

በዮሐንስ ወንጌል 10:10 ኢየሱስ ሲናገር፣ "እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው ሕይወት እንዲበዛላቸውም መጣሁ" ይላል:: እንዲሁም በ1ኛ ዮሐንስ 2:12-14 ስናነብ፣አሸናፊ ሕይወት ስለመኖር ተጽፎአል::

<u>አሸናፊ ሕይወት</u>፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት አግኝተው ዳግም የተወለዱ ሁሉ አሸናፊ ሕይወት እንደሚኖራቸው ተጽፎአል:: ይህ አዲስ ሕይወት የተሰጠን ለራሳችን ብቻ እንድንኖር ሳይሆን ለሌሎችም እንድንኖር ነው:: በዚህም የሕይወታችንን ምስክርነት ለሌሎች እናሳያለን ወይም ይተርፋል ማለት ነው::

ከቁ. 12-14 አንብብ:: ይህ ክፍል በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ስለሚያምኑ 3 ዓይነት ሰዎች ይናገራል:: ይኸውም:- ስለ ልጆች፣ስለ አባቶችና ስለ ወጣቶች ነው::

እነዚህ ሁሉ የአንዱ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው:: አንድ አባት አላቸው:: እርሱም እግዚአብሔር ነው:: የአንድ አባት ቤተሰብ ናቸው፤ ያውም የእግዚአብሔር ቤተሰብ:: የአንድ አገር ዜጋዎች ናቸው፤ ያውም የመንግሥተ ሰማይ ዜጋዎች:: እነዚህ ሦስቱም በእድሜ፣ በደረጃና በእድገት ልዩነት አላቸው::

በሥጋም ሆነ በመንፈሳዊ ደረጃቸው ልዩ እንደሆኑም መገመት ያስፈልገናል::

ቁ. 12 ና 13 ልጆች ሆይ ይላል:: እናንተ ልጆች ሆይ፣ የተትረፈረፈ ሕይወት መኖር ትችላላችሁ:: ምክንያቱም ክርስቶስን ስላመናችሁ የኃጢአት ስርየት ወይም ይቅርታ አግኝታችኋል:: ይህን ድንቅ ሕይወት የሰጣችሁን ጌታ ለሁሉ ሰው አስተዋውቁ፤ ዝም አትበሉ:: ዳዊትም በመዝሙር (32):1ና2 ኃጢአቱ የማይቆጠርበት ሰው ምስጉን ነው ብሎአል:: ደግሞም ልጆች ሆይ፣ አብን አውቃችኋልና ደስ ይበላችሁ፣ በመዝሙር(33):12 ላይ ተመልከቱ:: እውነተኛ አባታችሁን አውቃችሁ አባ አባት ብላችሁ ልትጮሁና ልትጠሩ የምትችሉበትን መንፈስ ቅዱስን አግኝታችኋልና፣ ገላ. 4:4-7:: ይህንን ለሁሉ ሰው ግለጹ:: ልጆች ሆይ የማደግን ጊዜ፣ የማወቅ ጊዜአችሁን ተጠቀሙ፤ ጠንካራ ለመሆን የቃሉን ወተት ብቻ ጠጡ፤ ማለትም የእግዚአብሔርን ቃል በብዛት አንብቡ፣ አጥኑ፤ 1ኛ ጴጥ. 2:2:: ተማሩ፣ ማቴ. 11:28-30 ማደግ ያስፈልጋችኋልና:: አባቶቻችሁን ጠይቋቸው መዝ(44):1-3 ምዕ.(78)1-8፤ ዘዳ. 32:7፤ 1ኛ ዮሐ. 4:4::

ቁ. 13ና14 አባቶች ሆይ ይላል:: አባቶች ከመጀመሪያ የነበረውን አውቃችኋልና:: ከመጀመሪያ የነበረና ያለ እግዚአብሔር ነው፣ ዘፍጥ. 1:1፤ ዮሐ. 1:1-2:: ከመጀመሪያ ከጥንት የነበረ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ሌላ የለም፣ ዘፀ. 3:14:: እግዚአብሔርን ማወቅ ጥበብ ነው፤ ምሳሌ 1:7፤ 9:10 ላይ ቅዱሱን ማወቅ ማስተዋል ነው ይላል:: እግዚአብሔር ለሙሴ ያለና የነበረ እኔ ነኝ ሲል ራሱን ገለጸ:: ስለዚህ አባቶች ሆይ፣ ብዙ ነገሮችን እግዚአብሔር ሲሠራና ሲያደርግ አይታችኋል፣ ብዙ ሰምታችኋል፣ ረጅም እድሜ በመኖር ብዙ አውቃችኋል፣ የእግዚአብሔርን ቃልም ብዙ ሰምታችኋል፣ ብዙ ተነግሯችኋል:: ስለዚህ አባቶች ሆይ፣ የተትረፈረፈ ሕይወት መኖርን ለልጆቻችሁ አስታውቁአቸው፣ ተናገሩ:: የእግዚአብሔርን ሥራ አስተ ምሩአቸው፣ አስታውቁዋቸው:: ለዚህ ነው እግዚአብሔር ያስቀመጣ ችሁ፣ ዘፀ. 12:26-27፤ ዘዳ. 6:20-25፣ መሳፍ. 6:13:: በጌታ በማመን የቆያችሁ፣ አባቶች የሆናችሁ፣ ቃሉ በእናንተ

ዘንድ ተጠብቆ የኖራችሁ የእምነት አባቶች፣ በእምነት ልጆች የሆኑትንና ገና በእድገት ላይ ያሉ ልጆችን አሳድጓቸው፣ ምከሯቸው፣ ዘዳ. 6፡6-9:: አባቶች ሆይ፣ በልጆች ዘንድ የበሰላችሁ ሁኑ፤ በጥበብ ተናገሩ፣ 1ኛ ቆሮ. 2፡6:: በዘመናችን ብዙ በመንፈሳዊ ነገር አባቶች የሆኑ፣ የቆዩ በመንፈሳዊ ሕይወት የበሰሉ የሉምና እናንተ በቤታችሁ፣ በጐረቤቶቻችሁ፣ በቤተ ክርስቲያናችሁና በአገራችሁም መንፈሳዊ አባት ለመሆን ተዘጋጁ:: እግዚአብሔር በሰማይ ታላቅ አባት ሲሆን፣ በምድር ላይ እግዚአብሔርን የምትወክሉ የምድር መንፈሳዊ አባቶች ሁኑ:: እግዚአብሔርን እንድትመስሉ ያስፈልጋል፣ 1ኛ ቆሮ. 11፡1::

ቁ. 13ና14 ጐበዞች ሆይ ይላል፣ ይህም ወጣቶች ማለት ነው:: በመንፈሳዊ ነገር ገና ኃይል ያላችሁ፣ በሥጋዊ ሁኔታ ገና ኃይል ያላችሁ ማለት ነው:: ብርቱዎች ስለሆናችሁ ደስ ይበላችሁ፤ ፊልጵ. 4፡4:: ሰይጣንን አሸንፋችኋልና ይላል የእግዚአብሔር ቃል:: የምታሸንፉበት ምሥጢር የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ ስለሚኖርና ቃሉን አጽንታችሁ ስለያዛችሁ ነው:: ቃሉን በቀንና በሌሊት ስለምታነብቡ፣ ስለምታጠኑም ነው፤ ኢያሱ 1፡8-9፤ መዝ. 1፡2-3:: በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ታሸንፋላችሁ:: ቃሉ ኃይል ይሰጣል:: ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉን እችላለሁ ብሉ፣ ፊልጵ. 4፡13:: የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ፣ ቈላ. 3፡16:: ለወንጌል ሥራና ለምስክርነት ኃይለኛ ለመሆን፣ ለመዘመር ኃይለኛ ለመሆን፣ ሌሎችን ለማስተማር ኃይለኛ ለመሆን የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ ውስጥ ይሙላ:: ታሸንፋላችሁ::

## አሸናፊነት በምን ይመጣል?

1. የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ ውስጥ ሲኖር ነው፣ 1ኛ ዮሐ. 2፡14፤ ዮሐ. 8፡37፤ ምሳ. 5፡38፤ መዝ.(119)፡9-14::
2. በጌታና በኃይሉ ችሎት ስትበረቱ ነው፣ ኤፌ. 6፡10::
3. ፈጣሪያችሁን በማወቅ ነው፣ መክብብ 12፡1::

4. በአሸናፊው ኢየሱስ ላይ በሙሉ ልብ በመደገፍ ነው፣ ዮሐ. 16:33፣ ምሳሌ 3:5::
5. ሳታቋርጡ በመጸለይ፣ 1ኛ ተሰ. 5:16-18::
6. ከልጅነት ዘመን ጀምሮ የጌታን ቀንበር መሸከምን በመለማመድ፣ ሰቆቃወ ኤር. 3:37::
7. ከኃጢአት በመሸሽ፣ ዘፍጥ. 39:7-14፣ 2ኛ ጢሞ. 2:22 ተመልከት::
8. ለአሸናፊዎች የተሰጠውን ተስፋ በመመልከት፣ ራእይ 2:7:: ልጆች ሆይ፣ አሸንፋችኋልና 1ኛ ዮሐ. 4:14::

ዓለምን ወይም የእግዚአብሔርን ፈቃድ፣
ቁ. 15-17 አንብቡ

በ1ኛ ዮሐንስ 2:15 ላይ ዮሐንስ ዓለምን አትውደዱ ሲል፣ በዮሐንስ ወንጌል 3:16 ላይ ደግሞ እግዚአብሔር ዓለምን ወዷልና ይላል:: እንግዲህ ወንጌል እርስ በርሱ የሚቃረን አይደለም:: ማወቅ የሚገባን የሁለቱ መጽሐፍ አሳብ የተለያየ መሆኑን ነው:: ዓላማና ግቡ ይለያያል:: በወንጌል ውስጥ እግዚአብሔር ዓለምን የወደደበት ምክንያት፣ ዓለምን ከኃጢአት ለማዳን ነው:: እግዚአብሔር ዓለምን የሚወድበት ምክንያት ሊያሳምራት ነው:: እግዚአብሔር ዓለምን የወደደበት ምክንያት ዓለምን ሁሉ ለመርዳት በማሰብ ነው::

ሰው ግን ዓለምን የሚወድደው ኃጢአት ሊሠራበት ነው:: ሰው ዓለምን የሚወድደው ሊያበላሽ ነው:: ሰው ግን ዓለምን የሚወድደው ለስስቱ ነው፤ ለራሱ ብቻ ነው::

በቁ. 15 ላይ ዓለምን አትውደዱ ብሎ ክርስቲያኖችን ያስጠነቅቃል:: ዓለም ምንድን ነው? ሁለተኛ ለምን አትውደዱ አለ?

1. ዓለም ሲል እግዚአብሔር የሠራቸውን ነገሮች አይደለም:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር እጅ የሚነጥቀንን ተድላና ኑሮ ነው:: እግዚአብሔርን የማይፈሩ ሰዎች የሚሠሩትን ኃጢአት

ነው:: ወይም ሰው ሠራሽ ዓለምን ነው:: በኃጢአት የተሸፈነ ዓለምን ነው:: እግዚአብሔርን መፍራት የሌለበት ዓለም ማለት ሲሆን፣ በዐመፅ ኃይልና በሰይጣናዊ አሠራር የሚመላለስ ዓለምን ያሳያል:: ከእግዚአብሔር ፍቅር በላይ ሌላ ነገር መውደድን ያሳያል:: በማቴዎስ 6:24 ለሁለት ጌቶች መገዛት አትችሉም ይላል:: ምንም ነገር ቢሆን ከእግዚአብሔር ፍቅር በላይ የሚሆን ከሆነ፣ ለእግዚአብሔር እንዳንታዘዝ የሚያደርገን ነገር ሁሉ ከክፉ ዓለም ስለሆነ ከእርሱ እንሽሽ::

2. ዓለምን አትውደዱ ያለበት ምክንያት:-

ሀ) የክርስቶስ ተከታይ ስለሆንህ ነው፣ ዮሐ. 17:14-16:: የዓለም ተከታይ አይደለህምና::

ለ) አንተና መላ አካልህ ያንተ አይደለም:: በዋጋ ተገዝተሃል፣ 1ኛ ቆሮ. 6:19-20፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነህ:: ሌላ ነገር ወይም የዓለም ኃጢአት በሕይወትህ እንዲኖር አያስፈልግም::

ሐ) ለእግዚአብሔር የተመረጥህ ውድ ሕዝብና ወገን፣ ካህንም ስለሆንህ ነው፣ 1ኛ ጴጥ. 2:9-10::

መ) አንተ እምነትህ (አዲስ ሕይወት) ከላይ መጣ እንጂ ከምድር ከዓለም አይደለም፤ ፊልጵ. 3:20:: ስለዚህ ኅብረትህ ከሰማያዊ አባትህ ጋር ይሁን እንጂ ከዓለም ጋር እንዳይሆን ተጠንቀቅ::

ቁ. 16 ዓለም ምን እንደሆነ 3 ነገሮችን ያመለክታል::

እነርሱም፣ የሥጋ ምኞት፣ የዓይን አምሮትና ስለ ገንዘብ መመካት ሲል ያስቀምጣል:: እነዚህ ሦስት ነገሮች በሰው ውስጥ የሚገኙ ዋና ነገሮች ሆነው ለኃጢአት ወይም ለፈተና ዋና ምንጭ ናቸው:: እስቲ እንመልከታቸው:-

## 1. የሥጋ ምኞት፣

ሥጋችን የውስጥ ሰውነትን ሁኔታ ይገልጻል። በሰውነታችን የሥጋ ፍላጐት አለ። እግዚአብሔር በሰውነታችን ውስጥ ፍላጐትን አስቀምጦአል። ለምሳሌ፣ ረሃብ ምግብ እንድንፈልግ፣ ጥማት ውኃ እንድንፈልግ፣ እንቅልፍን እንድናርፍ፣ የጋብቻ ፍላጐት የትዳር ጓደኛ እንድንፈልግ ያደርገናል። ፍላጐት የተፈጠረው ለመልካም ነው። ይህ መልካም ፍላጐት ግን በኃጢአት ምክንያት ተበላሸ። ዝቅተኛ ሆኖ ወደ ውድቀት ደረሰ። ያ መልካም ምኞት እየሞተ በቦታው ክፉ ምኞትና ፍላጐት በሰው ገባ፣ በዛ።

<u>ለምሳሌ</u>፣ አንድ ነገር ለማግኘት መፈለግ ጥሩ ሲሆን፣ ለማግኘት ያለ መንገዱ መሄድ፣ ከመጠን በላይ መፈለግና መመኘት ወደ ውድቀት ያደርሳል። እናታችን ሔዋን በዚህ ዓይነት ፈተና ወድቃለች፣ ዘፍጥ. 3:6። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰይጣን በሥጋ ምኞት ሊጥላቸው የሞከረ ብዙ ሰዎች አሉ። አንዳንዶች ወድቀዋል፣ ሌሎቹ ግን አሸንፈዋል።

1. አዳምና ሔዋን፣ ዘፍጥ. 3፤ እነርሱ ወደቁ።
2. ንጉሥ ዳዊት፣ 2ኛ ሳሙ. ምዕ. 11 እና 12 አንብብ።
3. ክርስቶስ ነበረ፣ ማቴ. 4፤ ሉቃስ 4:1-13:3 ኢየሱስ ክርስቶስ ድል አድራጊ ሆነ፣ አሸነፈ፤ ለእግዚአብሔር ክብር ይሁን።

ሰይጣን ሰዎችን በምን መንገድ እንደሚወድቁ ያውቃል። ስለዚህ ሁልጊዜም በምኞት ይፈትናል። አዳምና ሔዋን በምኞት ተፈትነው ወደቁ። ሰይጣን ኢየሱስ ክርስቶስን እንኳን በዚሁ መንገድ መፈተን ጀመረ። በመብል ፈትኖታል፣ ማቴ. 4:3-4። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም በእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ ብሎአል። እንዲሁም ለሚጠፋ ምግብ አትሥሩ፣ ዮሐ. 6:27 ብሎ የዲያብሎስን ራስ መትቶ አሸነፈ። ስለዚህ ምኞት የኃጢአት ጐዳና ሲሆን፣ ወደ ሞት ያደርሳል፣ ምሳሌ 14:2። ወደ መጥፎ ምኞት እንዳንደርስ እንጠንቀቅ፤ ያዕ. 1:15።

## 2. የዓይን አምሮት

ቁ. 16-17 ላይ ምኞት በዓይን በኩል ገብቶ በአንጐላችን በማረፍ አእምሮን የሚመርዝ የኃጢአት በሽታ ነው:: ለምሳሌ፣ ማየት መልካም ሲሆን፣ አይቶ መከጀል ግን ኃጢአት ነው፤ ማቴ. 5:28:: እንዲሁም ሀብት ማግኘት መልካም ሲሆን፣ የገንዘብ ፍቅር ግን የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው፣ 1ኛ ጢሞ. 6:10::

በኤድን ገነት ሔዋን በዚሁ ዓይነት የፈተና ዘዴ በጠላት ፈተና ወደቀች፣ ዘፍጥ. 3:6:: ሰይጣን ያንኑ ለክርስቶስ አሳየ፣ ማቴ. 4:8:: ክብርን አሳየ፣ ድሎትንና ምቾትን አሳየ:: ክርስቶስ ግን ድል አደረገው፣ አሸነፈው፤ ሉቃስ 4:2-13:: ሰይጣን ዛሬም ለክርስቲያን ከእግዚአብሔር ይልቅ ሀብትን፣ ክብርን፣ ኃይልን፣ ሥልጣንንና ግርማ ሞገስን በማሳየት እንዲያመልኩት ሊያደርግ እየሞከረ ነው:: የሥጋ ምኞት፣ የዓይን አምሮትም ቢሆን የእግዚአብሔርን ክብር ከመጨምር ይልቅ እንዲቀንስ የሚያደርግ ነውና እንጠንቀቅ::

## 3. በገንዘብ መመካት ቁ. 16-17

ሀብታም ሰው በማን ይመካል? በሀብቱ አይደለምን? አዋቂስ በእውቀቱ አይደለምን? በገንዘብ መመካት ትዕቢትን ያመጣል:: እኔነትንና ድፍረትን ሲያመጣ ሰውን መናቅ ይጀምራል:: ውጤቱ ምሳሌ 11:2 ላይ ያለው ውድቀት ነው::

እናታችን ሔዋን በዘፍጥ. 3:6 በዚህ ተፈተነች:: አዋቂና ጥበበኛ ለመሆን ወይም እንደ እግዚአብሔር ለመሆን፣ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ለማድረግ ኃይል ለማግኘት ፈለገች:: ከእግዚአብሔር በታች ተገዝታ ወይም በጥገኝነት ለመኖር አልፈለገችም:: እንደዚሁም ዛሬ ሰው ሀብት ካገኘ ወይም የተማረ ከመሰለው እግዚአብሔርን መካድ ይጀምራል:: እግዚአብሔር የለም ሊል ይጀምራል፤ መዝ. 11:1-6:: ሰው ሀብት ካገኘ ሁሉ አለኝ፤ እግዚአብሔር ለምንም አያስፈልገኝም ይላል:: ሰይጣን የክርስቶስን ችሎታ ለማየት ፈለገ፣ ማቴ. 4:5:: ዛሬም ሰዎችን በል ችሎታህን፣ ሀብትህን አሳይ ይላል:: አንተ

ከሁሉ በላይ ነህ። ሁሉም አለህ ይላል። ክርስቲያኖችን እንኳን ከማጥፋት አይመለስም። አንተ እኮ መስበክ ትችላለህ፣ መዘመር ትችላለህ፣ መጸለይ በጣም ትችላለህ። አንተ እኮ መንፈሳዊ ነህ፣ ከሌሎች ትበልጣለህ። ሁሉም መንፈሳዊ ስጦታዎች ባንተ አለ፣ ስለዚህ ሌሎች እንደ አንተ አይደሉም በማለት በክርስቲያኖች ጆሮ ሹክ ይልና በትምክህት ወይም በኩራት እንዲወድቁ ያደርጋል። የዋሁ ክርስቲያን በኩራት ተነፍቶ ሌሎችን መናቅ ይጀምርና በትዕቢት ጉድጓድ ይገባል፣ ምሳሌ 16:5።

ስለዚህ ክርስቲያን ሆይ፣ ገንዘብ ፈተና አይሁንብህ። ይልቁንም እንደ እግዚአብሔር ቃል ተጠቀምበት። የእግዚአብሔርን ለእግዚአ ብሔር ስጥ፤ ማቴ. 22:19-21። የመንግሥትን ለመንግሥት ስጥ፤ ሮሜ 13:6-7። አንተ ክርስቲያን አሥራት የእግዚአብሔር ነው። ለራስህ አትብላ። ምጽዋትና በኩራትም ስጠው። ወድዶ የሚሰጠውን ጌታ ይወዳልና፤ 2ኛ ቆሮ. 9:7።

ክርስቲያን ሆይ፣ አንተ በኃጢአት የረከስህ መሆንህን፣ (ሮሜ 3:23) እና መመካት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን አትርሳ። በዚያን ጊዜ አሸናፊ ትሆናለህ። የዓለምን ፍቅር በመከተል የእግዚአብሔር ፍቅር እንዳይለይህ ተጠንቀቅበት።

ቁ. 17፤ ዓለምና የዓለም ምኞት ያልፋል። ይህም የሥጋ ምኞት፣ የዓይን አምሮት፣ በገንዘብ መመካት፣ ሁሉም ያልፋል። ጊዜያዊ ነገሮች ብቻ ናቸው። የማያልፈው የእግዚአብሔር ቃልና እንዲሁም በእምነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርጉት ብቻ ናቸው። እነርሱ ለዘላለም ይኖራሉ፣ አይጠፉም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙ ከሞት በኋላ ወይም ከዚህ ዓለም በኋላ እንኳን ለዘላለም ይኖራሉ፣ ዮሐ. 6:28-29፣ ምዕ. 11:25-26። አንተስ ለዘላለም የመኖር ተስፋ አለህ?

ሠ) የሐሰት ሕይወት፣ 1ኛ ዮሐ. 2:18-27 አንብብ

ይህ ጥቅስ ስለ መጨረሻው ሰዓት ይነግረናል:: በዚህ ቦታ ላይ ስለ መጨረሻው ዘመን ሳይሆን ስለ መጨረሻው ሰዓት እየተናገረ መሆኑን ልብ በል::

ቁ. 18፤ መጽሐፍ ቅዱስ መጨረሻ ሲል የማለቂያ ጊዜ ወይም ሰዓት መሆኑን ማስታወቁ ነው:: መጨረሻ ሰዓት ከዘመንም ከጊዜም ያጠረ ነው:: መጨረሻ ሰዓት ማለት ጊዜው አጭር ነው ማለት ነው::

1. መጨረሻ ሰዓት ነው ሲል ጠቅላላ የጸጋ ዘመን ወይም የቤተ ክርስቲያን ዘመን ሲሆን፣ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ነው፣ ገላ. 4:4::
2. መጨረሻ ሲል ኢየሱስ የተጠየቀበትን የእርሱን ዳግም መምጣት ያመለክታል፣ ማቴ. 24:3::
3. መጨረሻ ሰዓት ሲል የፍርድ ጊዜን ያሳያል:: ክርስቶስ ጻድቃንን ወደ መንግሥቱ፣ ኃጢአተኞችን ወደ ገሃነመ እሳት ፍርድ የሚልክበት ጊዜ ነው፣ ማቴ. 25:31-46:: ስለዚህ አንባቢ ሆይ፣ የምንኖርበት የመጨረሻ ሰዓት መሆኑን አስብ:: አሁን ድንገት መጨረሻ ቢመጣ ያንተስ ዕድል የት ይሆን? ክርስቶስን በእምነት ተቀብለህ ከሆነ ወደ ዘላለም ሕይወት፣ ክርስቶስን በእምነት ያልተቀበልህ ከሆነ ወደ ዘላለም ቅጣት መሄድህን ተገንዘብ::

ቁ. 18ና19 አንብብ:: በዚህ ቦታ ስለ ሁለት ዓይነት ተቃዋሚዎች ይናገራል:: ያውም ተቃዋሚና ተቃዋሚዎች እያለ ነው::

በመጀመሪያ ስለ ተቃዋሚዎች እንመልከት፣

I ተቃዋሚዎች:- ተቃዋሚዎች ሲል ብዙዎች እንደሆኑ እንወቅ:: እነዚህ ተቃዋሚዎች እነማን ናቸው? ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ የእግዚአብሔርን ዓላማና እውነት የሚቃወሙ፣

የእግዚአብሔርን ቃል መልእክት የማይቀበሉ ተቃዋሚዎች ተብለዋል::

1) ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ተቃዋሚዎች የተናገረውን በማቴ. 23:34-36 ተመልከት::

2) በሙሴ ዘመን ስለ ነበሩት 2ኛ ጢሞ. 3:8::

3) በነቢዩ በኤልያስ ዘመን ስለ ነበሩት ነገሥታት፣ 1ኛ ነገ. 18:22-40::

4) በአሞጽ ዘመን፣ አሞጽ 7:12-17:: እንደዚሁም ብሉይ ኪዳን ስለተቃዋሚዎች በብዙ ይነግረናል::

በአዲስ ኪዳንም የሐሰት ሰው ተብዬዎች በሁሉ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ ነበሩ እናያለን::

1) በገላትያ ቤተ ክርስቲያን የሐሰት አስተማሪዎች ወይም የሐሰተኞች ወንድሞች የተባሉ ነበሩ፤ ገላ. 1:7:: የክርስቶስን ወንጌል የሚያጣምሙ፣ ምዕ.2:4:: ባሪያዎች ሊያደርጉ ሾልከው በስውር የገቡ የሐሰት ወንድሞች፤ በቄላስይስ የክህደት ሰው፣ ምዕ. 2:3

2) በጢሞቴዎስ ዘመን የሚያስቱ መናፍስትን የሚያደምጡ፣ 1ኛ ጢሞ. 4:1፣ 2ኛ ጢሞ. 3:13:: እያሳቱና እየሳቱ የሚመጡ ክፉዎች::

3) በዮሐንስ ዘመንም ኖስቲክ የተባሉ የሐሰት ነቢያት ነበሩ:: የክርስቶስን በሥጋ መወለድ እየተቃወሙ፣ ክርስቶስ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ከሆነ፣ እርሱ እግዚአብሔር ከሆነ እንዴት ሥጋ ይለብሳል? ይሉ ነበረ:: ሥጋ ርኩስ ነው፤ መንፈስ ግን ቅዱስ ነው፣ ቅዱስ እግዚአብሔር ርኩስ የሆነ ሥጋ መልበስ አይችልም:: ሥጋ ከለበሰ አምላክ ሊሆን አይችልም:: ሰውንም ለማዳን ችሎታ የለውም የሚሉ ትምህርቶችን ያስተምሩ ነበር:: ወንጌልን የሚቃወሙ መምህራን ነበሩ:: «እነዚህ ከእኛ ወጡ፤ ከእኛ ጋር ነበሩ::» ይላል::

ዛሬም በዘመናችን ከእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበሩ፣ ከቤተ ክርስቲያን ወጥተው ወንጌልን እንደፈቃዳቸው እየተረጐሙ የሚያስቱና የሳቱስ ስንት ናቸው? በዘመናችን ብዙ ተቃዋሚዎች አሉ:: የስሕተት ትምህርትን አብዝተው ያራምዳሉ:: በእኛ ዘመን ካሉት አስመሳይ ክርስቲያኖች ውስጥ፣

1ኛ/ አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን እኩል አንድ አምላክ መሆኑን የሚክዱ ስንት ናቸው? ቁ. 20-24 አንብብ::

መንፈስ ቅዱስን ቅዱስ ቅባት ብለው አብንና ወልድን በክህደት ያስቀምጣሉ:: ማቴ. 28:18-20፤ ዘፍጥ. 1:26 በመልካችን በምሳሌያችን እንፍጠር፤ ዘፍጥ. 11:6-7 እግዚአብሔርም አለ ኑ እንውረድ፤ 2ኛ ቆሮ. 13:14 ያለውን ሥላሴን የሚክዱ ስንት ናቸው?

2ኛ/ አብ ብቻ ነው አምላክ፤ ወልድ ግን አይደለም የሚሉትን የይሖዋ ምስክሮችን በምን ቦታ ታስቀምጣለህ? ቁ. 23-24

3ኛ/ ወልድ ብቻ ነው አምላክ፣ አብ ግን አይደለም ብለው የሚከራከሩትን ኢየሱስ ብቻ ወይም (Only Jesus) የተባሉትን የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አማኞችንስ የት ታስቀምጣለህ? 2ኛ ዮሐ. 1:9-10 ተመልከቱ:: እንደ ኢየሱስ ዓይነት ትምህርት የማያስተምር ሁሉ ተቃዋሚ ነው::

4ኛ/ መንፈስ ነን የሚሉትንስ ታውቃቸዋለህን?

5ኛ/ አምላክ ነን:: ከአንድ ፍጥረት ወደ ሌላ እንለወጣለን የሚሉትን የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አራማጆችንስ (New Age Movment) ምን ትላለህ?

6ኛ/ የክርስቶስን ትምህርት ሳይሆን ሰንበትን ብለው ሙጥኝ የሚሉ አድቬንቲስትን ታውቃለህ? ዋና አካሉን ክርስቶስን የረሱትን ቈላ. 2:16-19:: ራስ ማን ነው? ኤፌ. 5:23 ክርስቶስ ነው:: እርሱ ነው ወደ አብ የሚያመጣ፣ ዮሐ. 14:6፤ ማር. 2:27-28:: እንደዚሁም የክርስቶስን ትምህርት የማያስተምሩትን ሁሉ አስብ፤ እነርሱ ተቃዋሚዎች ናቸው:: አንድ ተቃዋሚ የተባለ የተቃዋሚዎች መሪ እነርሱ የሐሳዊ

መሢሕን መምጣት የሚጠባበቁና መንገድ አዘጋጆች ናቸው:: ሌሎችም ክርስቶስን የሚክዱ ጭምር የተቃዋሚ አገልጋዮች ናቸው:: አንባቢ ሆይ፣ አንተስ ከእነዚህ ውስጥ አለህበት ወይ?

II ቁ.18-22 ስለ ተቃዋሚ አንብብ

ይህ ተቃዋሚ የተባለው ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ስም አለው:: ከእነዚህ በጥቂቱ ለምሳሌ ያህል፣ ሐሳዊ መሢሕ፣ የጥፋት ልጅ፣ የዓመፅ ሰው፣ እኔ እግዚአብሔር ወይም አምላክ ነኝ ባይ፣ 2ኛ ተሰሎ. 2:3-12:: እኔ ክርስቶስ ነኝ (ማቴ. 24:5) የሚል አውሬ የተባለ፣ ራእይ 13:1፤ ራእይ 19:20:: እርሱ ማን ነው? እርሱ ገና በዓለማችን የሚመጣ የሰይጣንን ኃይልና ሥልጣን የለበሰ ሙሉ ዓለምንና የዓለምን ሥልጣን በእጁ የያዘ ሰው ወይም ፍልስፍና ያለው ነው::

ክርስቶስ በዚህ ዓለም በነበረበት ዘመን ክርስቶስን እንዴት አድርገን እናጥፋ ብሎ ለተጨነቀ ዓለም ወይም ካህናትና ገዢዎች መላ ያስገኘ አንድ ሰው ነበር:: እርሱም ይሁዳ የአስቆሮቱ ነበር:: እርሱን ሰይጣን እንደ ተጠቀመበት ሁሉ፣ እንዲሁም በአሁኑ ዓለም ወይም ሕዝብ ሰላምንና አንድነትን እንፈልጋለን ብለው ለሚጨነቁ መላ የሚሰጥ አንድ ይዘትና ዓላማ ያለው የዓለም ገዢና ራስ የሆነ ሰው ወይም ፍልስፍና እንደሚነሣ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል፣ 2ኛ ተሰሎ. 2:4:: እርሱ ሲመጣ በራሱ ፈቃድ ይመጣል:: ሁሉም ይቀበሉታል፣ ዮሐ. 5:43:: ሁሉን እንደ ፈቃዱ ያደርጋል፣ ዳንኤል 11:36:: ሥራውም ክርስቶስን መቃወም ብቻ ሳይሆን፣ የክርስቶስን ሥራ መፈታትንም ጭምር ነው::

<u>ይህ መቼ ነው የሚሆነው</u>? መልሱ:- በመጨረሻው ዘመን::

የእርሱ መጨረሻ ምን ይሆናል? <u>መ</u>ልሱ ራእይ 19:20፣ 20:10ና15 ተመልከት::

ክርስቶስ እኛን ለማዳን በሥጋ መምጣቱን የሚክድ ሁሉ እርሱ አምላክ መሆኑንም የሚክድ (ኢሳ. 9:6፤ ዮሐ. 20:28፤

ፊልጵ. 2:5-11፤ ዕብ. 1:8) ዛሬም የተቃዋሚ መንፈስ ያለበት ነው፣ 1ኛ ዮሐ. 4:3:: የእርሱ ደጋፊም ነው::

የአሁን የክርስቶስ ተቃዋሚዎች ለወደፊት የክርስቶስ ተቃዋሚ ሆነው የሚሠሩ ከሆነ፣ ለእውነተኛ ክርስቲያኖች ምን ተስፋ አላቸው? እንዴትስ መቃወምና መከላከል ይችላሉ? መልስ አለ፣ ቀጥሎ ያሉትን ተመልከት:-

ይህን የሐሰት መንፈስና ሕይወት የምንከላከልባቸው ሦስት መከላከያዎች ተሰጥተውናል:: ሦስቱንም አውቀን በእምነት እንጠብቅ:: እነርሱም ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ናቸው:-

1ኛ መከላከያ፣ ቁ. 20 ና 27 አንብብ:: እርሱም ቅዱስ ቅባት ወይም መንፈስ ቅዱስ ነው:: በውስጣችን የሚያድር መንፈስ ቅዱስ ማለት ነው:: ጠባቂያችን መንፈስ ቅዱስ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ከቅዱስ ቅባቱ ተቀብላችኋልና ሁሉንም ታውቃላችሁ ይላል:: ስለዚህ ሐሰተኛ ትምህርትን ለይታችሁ ማወቅ ትችላላችሁ ማለት ነው:: በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ አማኝ ለይቶ የማወቅ ችሎታ ተሰጥቶታል:: ስለዚህ ክርስቲያን እውነተኛውንና ውሸተኛውን ትምህርት ለይቶ ለመፍረድ ይችላል:: ምክንያቱም እውነትን የሚገልጽና የሚፈርድ እውነተኛ መንፈስ ቅዱስ ነው:: መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ስለተሰጠንና በውስጣችን ስለሚኖር እውነትን ይገልጽልናል፤ ዮሐ. 16:13:: በውስጣችንም የሚኖረው ለእውነት ሊፈርድ ነው፣ ዮሐ. 15:26-27:: ስለዚህ እውነተኛ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል እያነበበ እውነትን ከእግዚአብሔር ይጠብቃል:: እርሱም ይገልጥለታል:: የጌታ ልጅ ስለሆነ፣ ዮሐ. 1:12:: መንፈሱን በልቡ ልኮአልና፣ ገላ. 4:6፣ ዮሐ. 7:38:: በክርስቶስ ስናምን ለእግዚአብሔር ካህናት እንሆን ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ይቀባናል፣ ያትመናል፣ኤፌ. 1:13:: 1ኛ ዮሐ. 2:27 ተመልከቱ:: ከክርስቶስ የተቀበላችሁት መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ አስተማሪ ነው ይላል:: እውነትን ከውሸት ለይተን እግዚአብሔር የሚወደውንና የሚጠላውን ለይተን እንድናውቅ ያስተምረናል:: አንባቢ ሆይ፣ እውነተኛ ሃይማኖትን ለይተህ ታውቃለህ?

ይህንን ቁጥር አንዳንድ ሰዎች ሲጠቅሱ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ሄዶ መማር አያስፈልግም፤ መንፈስ ቅዱስ ያስተምራችኋል እያሉ ይተረጉማሉ:: በዚህ ቦታ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ጉዳይ ሳይሆን፣ ስለ ሐሰተኛ አስተማሪዎችና ስለ ተቃዋሚዎች ማለት ስለ ሐሳዊ መሢሕ ነው የሚያስተምረው:: መንፈስ ቅዱስ የሐሰተኛን ኃይል የምንከላከልበት መሣሪያችን ነው::

<u>2ኛ መከላከያ</u>፣ ቁ. 24 አንብብ:: ከመጀመሪያ የሰማችሁት ይላል:: የሰሙት ቃሉን ነበረ:: እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ማለት ነው:: በመጀመሪያ ወደ እምነት ያመጣችሁ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ኤፌ. 1:13:: ወደ እምነት የመጣነው የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ቅዱስ የማይናወጡ ጽኑ መሠረቶች ስለሆኑ ነው:: በእግዚአብሔር ቃል ላይ መሠረቱን የጣለ ሰው ምንም አይናወጥም፣ ማንም ሊያናውጠው አይችልም፤ ማቴ. 7:24-25:: ውሸት አያናውጠውም፤ ሰይጣን አያናውጠውም:: ሁልጊዜ ቃሉን ስለሚመገብ ጠንካራ ይሆናል፣ መዝ. 1:1-6:: በሕይወቱ ብርሃን ስለሚያልፍ ውሸት ሲመጣ በቀላሉ ያውቀዋል:: ውሸትንና እውነትን በቀላሉ ይለያል:: አንባቢ ሆይ፣ መጽሐፍ ቅዱስ (ቃሉ) ለሕይወትህ መሪ ይሁን፤ መዝ. (119):105:: ሁልጊዜ ከቃሉ አትለይ:: በቀንና በሌሊት አንብበው፣ ኢያሱ 1:8-9::

<u>3ኛ መከላከያ</u>፣ ቁ. 25 አንብብ:: የተሰጠን ተስፋ ወይም የዘላለም ሕይወት ነው ይላል:: እምነት እንደ መልሕቅ ነው:: መልሕቅ መርከብ እንዳይናወጥ በባሕር ላይ አጽንቶ እንደሚይዘው ሁሉ፣ የዘላለም ተስፋም እንደዚሁ ነው፤ ዕብ. 6:19:: የምንወርሰው የዘላለም ሕይወት ተስፋም እንደዚሁ አጽንቶ የሚይዝ ነው:: በክርስቶስ ሞትና በፈሰሰው ደም የተረጋገጠ ተስፋ ወይም የዘላለም ሕይወት ሙሉ ዋስትና አለው:: ስለዚህ ይህ ተስፋ ፍርሃትን ሁሉ ያስወግዳል:: ከዚህ ከምድር ጀምሮ ወደ ሙሉ ሕይወት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊያደርስህ ፍጹም ጽናትንና ድፍረትን እየሰጠ ይመራሃል፣ ሮሜ 8:1፤ መዝ. 23:1-6:: የዘላለም ሕይወት ወራሽ ነህና ተስፋውን ያዝ:: በዚህ ምክንያት ማንም ቢመጣ አሸናፊ

ሕይወት ይኖርሃል። አሁንም ወደ አሸናፊ ሕይወት ውስጥ ልትገባ ትችላለህ። አንባቢ ሆይ፣ የዘላለም ሕይወት ተስፋ አለህ ወይ?

## ረ) የወደፊት መጪ ሕይወት፣

1ኛ ዮሐ. 2:28 - 3:1-3 አንብብ። እነዚህ ቁጥሮች ስለ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት ይናገራሉ። የክርስቶስ ዳግም መምጣት ለነገር ሁሉ መጨረሻ ይሆናል። ለነገር ሁሉ መጀመሪያ እንደ ነበረ እንዲሁም መጨረሻ ይሆናል።

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ የክርስትና ሃይማኖት እንደ ጀመረ ሁሉ፣ እንዲሁም ወደዚህ ዓለም መጥቶ የክርስትና ሃይማኖትን ያበቃል ወይም ይጨርሳል፣ ያጠቃልላል። የዓለም ፍጥረት ሁሉ የተጀመረበት ጊዜ እንደ ነበረ ሁሉ የሚያልፍበት ዘመን እየመጣ ነው፣ 1ኛ ዮሐ. 2:17፤ ማቴ. 24:35። እምነታችንና ተስፋችን ለዚህ ዓለም መጨረሻ ሆኖ ለሚመጣው ዓለም ግን ጅማሬ ይሆናል። ክርስቶስ ተመልሶ ይመጣል።

ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሞቶ እንደ ተነሣ ካመንን፣ እንዲሁም በእርሱ ያመኑትን ወደ እርሱ ሊወስድ ይመጣል፣ ዮሐ. 14:2።

ክርስቶስ በእርሱ ባላመኑትና እርሱን በሚጠሉት ላይ ሊፈርድ ይመጣል፣ ራእይ 6:15-17። አንተስ እንዴት ትሆናለህ?

ቁ. 28፣ ጌታ በድንገት ከሰማይ ይገለጣል፣ 1ኛ ተሰ. 4:13 - 5:3 አንብብ። 1ኛ ቆሮ. 15:51-57። ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ እኛም በፊቱ እንገለጣለን ወይም እንቆማለን። ይህ ጉስቋላ ሰውነታችን ይቀራል። እኛም ተለውጠን እንደ እርሱ እንሆናለን፤ እርሱን እንመስላለን።

በክርስቶስ መምጣት እኛ በፊቱ የምንቆመው ለሁለት ምክንያት ነው።

1ኛ/ ለደኅንነታችን ፍጻሜ ይሆናል። በምድር የጀመርነው የእምነት ደኅንነታችን በፊቱ ይጸድቃል። የልጅነታችን ዓላማ ግቡን ይመታል፤ ወደ ፍጻሜም ይደርሳል። ከዚያ ጀምሮ እንደ እርሱ እንሆናለን፣ ወደ ቤቱም እንደርሳለን።

2ኛ/ በፊቱ እንገለጣለን:: በዚህ ዓለም የሠራነውን የሥራችን ወይም አገልግሎታችን ውጤት መቀበያችን እንዲሆን ነው:: ሥራችን የሚጸናበት ወይም የሚቃጠልበትና ዋጋችንን የምንቀበልበት ጊዜ ይሆናል:: ለሥራችን የፍርድ ጊዜ ይመጣል፣ 1ኛ ቆሮ. 3:12-15፤ 1ኛ ዮሐ. 2:28 - 3:1-3:: በእነዚህ ቁጥሮች ስለ ክርስቶስ ዳግም መምጣትና የአማኞች ሁኔታ ምን እንደሚሆን ይገልጻሉ:: በክርስቶስ ዳግም መመለስ የክርስቲያን ሁኔታ ምን እንደሚሆን በአምስት መንገድ ተገልጿል::

1ኛ/ ቁጥር 28፣ በጌታ መምጣት የማያሳፍር እምነት ይሆንልናል::

በምድር ስንኖር ስለ እምነታችን ትልቅ ሐፍረት ተሸክመን ነበር:: እርሱ ሲመጣ ግን ስለ እምነታችን ትልቅ ድፍረት፣ እረፍትና መጽናናት ይሆንልናል:: በምድር እንደ በግ እንቆጠር ነበር፣ ሮሜ 8:36:: ጌታ ሲመጣ ግን እንደ ሰባ እምቦሳ እንፈነጫለን፣ ሚልክ. 4:2-3:: ስለዚህ ዛሬ በእርሱ እንኑር፣ ዮሐ. 15:7-8:: ብዙ ፍሬም እናፍራ:: ዛሬ በአግባብ እንደ ጌታ ፈቃድ ባንኖር ፍርሃትና ሐፍረት ይሆንብናል::

2ኛ/ <u>ቁ. 29 አንብብ:: በጌታ መምጣት ከእርሱ መወለዳችን ይረጋገጣል::</u>

በጌታ በማመናችን በመንፈስ ቅዱስና በቃሉ አማካይነት ከእርሱ መወለዳችን ይረጋገጣል:: በሕይወታችን እግዚአብሔርን የመምሰል ባሕርይ እንደ ነበረን፣ እንዲሁም በሕይወታችን የጽድቅ ፍሬ እንዳለን ይገለጽልናል:: በዚያን ጊዜ የእውነተኛ ክርስቲያን የጽድቅ ፍሬ መሆኑን ሳይሆን የእግዚአብሔር ባሕርይ ጽድቅ በእኛ መኖሩ ይገለጻል ወይም ይታያል:: በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ለፍጥረት ሁሉ ጽድቁን ሲገልጽ፣ የእኛም ሕይወት እንደ እርሱ ጽድቅን ይገልጻል::

# ምዕራፍ ሦስት

3ኛ/ <u>በጌታ መምጣት ስማችን ይጸናል</u>፣ ምዕ. 3 ቁ.1

ስለ ስማችን በሉቃስ 10:20፤ ራእይ 3:5 ና12፤ ምዕ. 20:15 እናገኛለን:: ስም ለማግኘት መወለድ አለበት:: ሰው ከተወለደበት ባሕርይን ይወስዳል:: እኛም ከእግዚአብሔር የተወለድን ከሆነ፣ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ስለምንቀበል አንድ ስም አለን:: ያውም የእግዚአብሔር ልጆች መባላችን ነው:: ይህ ስም ምን ያህል ደስታና መጽናናት እንደሚሰጥ ቀምሳችሁ እዩ:: ይህ ስም ወይም የእግዚአብሔር ልጆች መባል በዓለም ላይ በክርስቶስ አምነን ስንመላለስ ትልቅ ለውጥ ያስከትላል:: በክርስቶስ አምነው ልጆቹ የሆኑት ሁሉ ሁለት ዓይነት ፍጥረት ወይም ባሕርይ አላቸው::

ሀ) ለአዲስ ልደት በመንፈስ ቅዱስ ስለ ተወለድን የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ባሕርይ ይኖረናል፤ ሮሜ 8:9-10::

ለ) በሥጋ ለዚህ ዓለም ስለ ተወለድን ሥጋዊ ባሕርይ ደግሞ አለን ማለት ነው:: ይህ ባሕርይ በጣም አስቸጋሪ ነው፤ ሮሜ 7:19-25 ተመልከት:: ይህ ሥጋዊ ባሕርይ ግን የሚሸነፍ ዓይነት ነው:: በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ከአሸናፊዎች እንበልጣለን፤ ሮሜ 8:37:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጅ መባል ከሁሉም ይበልጣል::

ክርስቶስ በዚህ ዓለም በነበረ ጊዜ ዓለም በእርሱ ሁኔታዎች እጅግ ትደነቅ ነበር፤ ማቴ. 12:23፤ ምዕ. 7:28:: እንዲሁም ዛሬ ዓለም በጌታ ተከታዮች ሁኔታ እየተደነቀች ናት፤ 1ኛ ጴጥ. 4:4-5:: በዚያን ጊዜ ግን ፍጥረት ሁሉ በልጅነታችን ይደነቃል፤ ሮሜ 8:19::

4ኛ/ <u>በጌታ መምጣት እንለወጣለን</u>፣ ቁ. 2ን አንብብ::

እርሱን እንመስላለን:: ዛሬ አንድ ሰው ጌታን በእምነት ሲቀበል ውስጣዊ ሕይወቱ ይለወጣል:: ውስጣዊ ሕይወቱ የእግዚአብሔርን ባህርይ ስለሚያገኝ፣ ያንን ሰው ዓለም አይታ ምን ሆነሃል? ተለውጠሃል እኮ? ትላለች:: ይህም ውስጣዊ ሕይወቱ ስለ ተለወጠ ነው፣ ሮሜ 8:29:: ጌታ ሲመለስ ግን

የውጭ ሕይወታችን እንኳን ይለወጣል፤ ማቴ. 13:43:: ጌታ ወደ ምድር መጥቶ በመወለድ የእኛን ሥጋ ለብሶ እንደ ነበረ ሁሉ፣ እንዲሁም በጌታ ሁለተኛ መምጣት እኛም የእርሱን መልክ መንፈሳዊ መልክ እንለብሳለን:: ደግሞ የክርስቶስን የፊተኛውን መምጣት በእምነት ማየት እንችላለን:: የጌታን ዳግም መምጣት ግን በእርግጥ ፊት ለፊት በዓይናችን እናየዋለን:: እንደ እርሱም እንሆናለን፤ 1ኛ ቆሮ. 13:12::

5ኛ/ <u>በጌታ መምጣት ፍጹም ንጽሕና እናገኛለን፣</u> ቁ. 3 አንብብ::

ዛሬ የክርስቶስን መገለጥ ተስፋ የምናደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደ ነበረ ራሳችንን በንጽሕና እንጠብቅ:: እርሱ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ብሎናልና፣ 1ኛ ጴጥ. 1:15-16:: ስለዚህ ዛሬ በእርሱ የተወለድን በጽድቅ፣ በቅድስና፣ በንጽሕና መልካም ሥራ እየሠራን መምጣቱን በተስፋ እንጠባበቀው:: ዘውድ መጫን ከመከራ በኋላ ነውና ተብሎአልና:: መከራን ለመቀበል አንፍራ፣ 2ኛ ጢሞ. 1:9፤ ምዕ. 4:5፤ ምዕ. 3:12፤ ፊልጵ. 1:28-29:: ኃጢአትና ተንኮል በሌለው ኑሮ እንኑር:: እርሱን እንምሰል:: በአሁኑ ሕይወት እርሱን ከመሰልን፣ በመጭውም ሕይወት እርሱን እንመስላለን::

## ለ) <u>አሸናፊው ሕይወት፣ 1ኛ ዮሐ. 3:4-10 አንብብ</u>

ለክርስቲያኖች አሸናፊ የሆነ ጌታ ስላላቸው ኃጢአትን ማሸነፍ ይችላሉ:: አሁን ባነበብናቸው ቁጥሮችና ቀደም ብሎ ባሉት ቁጥሮች መሠረት የክርስቶስን ዳግም መምጣት ተስፋ አድርጐ የሚጠብቅ ሰው ሁሉ ኃጢአትን ማድረግ እንዴት ይችላል? የጌታ ዳግም መምጣት ለክርስቲያን ትልቅ ተስፋ፣ ትልቅ መጽናናትና ንጽሕና ስለሆነ፣ ንጽሕና እየሰጠ መንፈስ ቅዱስ እያደሰ ሳለ፣ ታዲያስ ክርስቲያን ኃጢአትን ማድረግ ወይም መሥራት ይገባዋልን? ይላል:: መልሱም:- ኧረ አይሆንም:: ልጆቼ ኖችሁ አይሆንም ይላል፤ 1ኛ ዮሐ. 2:1፤ 3:4,9:: ክርስቲያን ከኃጢአት ጋር ጓደኝነት የለውም፣

ዝምድናም አያስፈልገውም:: ለምን ኃጢአት ማድረግ እንደሌለበት 4 ምክንያቶች እንመለከታለን::

1. ኃጢአትን መሥራት ወይም ማድረግ ከሕግ ውጭ ነው ይላል፣ ቁ. 4 አንብብ:: ዐመፅ ነው:: የማን ሕግ? መልሱ የእግዚአብሔርና የሰውም ሕግ ማለት ነው:: ኃጢአት ማድረግን እግዚአብሔር ይጠላል፣ ኅብረተሰቡም ይጠላል፣ መንግሥትም ይጠላል:: ኃጢአት ከሰው ባሕርይ ከሰው ውስጥ የሚወጣ ያለመታዘዝ ምልክት ነው:: ለእግዚአብሔር እምቢተኝነት ነው:: በክርስቶስ ለምናገኘው አዲስ ሕይወት አቋም ተቃራኒ ነው:: ኃጢአት ሕግን ብቻ ሳይሆን ሕይወትንም ይጐዳል::

2. ኃጢአትን ማድረግ ምክንያት የሌለው ጉዳይ ነው:: ክርስቶስ ኃጢአትን ሊያስወግድ ስለ መጣ ለምን እንፈቅድለትም? ቁ. 5 አንብብ:: ክርስቶስ በውስጣችን ካለ ኃጢአትን ከእኛ አውጥቶ ሊያጠፋና አዲስ ሕይወት፣ አሸናፊ ሕይወት ሊሰጠን ይችላል:: ክርስቶስ አስቀድሞ ኃጢአትን በመስቀል ላይ ወግቶ ገድሎታል፤ ኤፌ. 2:16፤ ቆላ. 2:14-15:: ስለዚህ በክርስቶስ የሞተ ኃጢአት፣ ሕይወት ያለውን ክርስቲያን ማሸነፍ የለበትም:: ክርስቶስ በፊተኛው መምጣቱ ከኃጢአት ዕዳ አድኖናል:: በሁለተኛው መምጣቱ ከኃጢአት መኖሪያ ያድነናል:: የክርስቶስ መምጣት ሁሉንም ኃጢአት ሊደመስስ ነው:: አንባቢ ሆይ፣ አንተስ ከኃጢአት ነፃ ነህን?

ቁ. 18 አንብብ:: ወደ መጨረሻ ያለውን ትኩረት አድርገህ ተመልከት:: ክርስቶስ በአንደኛ መምጣቱ ኃጢአትን ከአማኝ ልብ ሊያጠፋ ሲሆን፣ በዳግመኛ መምጣቱ ደግሞ ኃጢአትን ከዓለም ሊያጠፋ ሊያስወግድ ነው::

ዛሬ ክርስቲያኖች ኃጢአት ማድረግን የምንወድ ከሆነ በጌታ ሳናምን በፊት ያደረግናቸው ኃጢአቶች ገና አሉ ማለት ነው? ጌታ በጌታ ፊት ይታሰባል ገና አልተደመሰሰም ማለት ነው? ጌታ ውሸተኛ አይደለም:: እንዲህ ይላል መዝ. 103:12,13፣ ሚክ. 7:19 እንግዲያውስ የፊተኛው ኃጢአት የጠፋልን ከሆነ፣ ለምን እንደገና ኃጢአት እናደርጋለን? እንጥላው እንጂ:: አንዳንዶች

ጌታ ከኃጢአት ሊጠብቀን አይችልምን? ይላሉ:: አዎን፣ ጌታ ከፈቀድንለት ሊጠብቀን ይችላል:: እስከ መጨረሻ ቀን ድረስ ያለነቀፋ ይመራናል፣ ፊልጵ. 4:7:: ፊልጵ. 1:6፣ 1ኛ ተሰ. 5:23 ይሁዳ 1:24-25 ተመልከት:: ግን ያንተን ነፃ ፈቃድ ይፈልጋል::

3ኛ/ ኃጢአት ማድረግ መንፈሳዊነት ነውን? ቁ. 6-8 አንብብ::

መልሱ አይደለም ነው:: ኃጢአትን ማሸነፍ ብቻ ነው መንፈሳዊነት:: በክርስቶስ ያገኘነው አዲስ ሕይወት የኃጢአት ዕቃ መሆን የለበትም፤ የጽድቅ ዕቃ ነው እንጂ፤ ሮሜ 6:13:: እኛ ኃጢአትን አሸንፈን በጽድቅ እንድንሞላ የጌታ ፈቃድ ነው፤ ሮሜ 12:1-2::

ቁ. 6. ኃጢአትን የሚያደርግ አላየውም አላወቀውም ይላል:: አንድ ሰው በእምነት ከጌታ ጋር ሳይገናኝ ለሰው ወይም ለጓደኛ ወዳጅነት ይምሰል ብሎ፣ ክርስቲያኖችን ለማታለል ወደ ጌታ የመጣ አስመስሎ በመካከላቸው ተቀላቅሎ ከሆነ ኃጢአትን ድል ማድረግ አይችልም:: ስለዚህ እርሱ ራሱ ከጌታ ጋር በእርግጥ መገናኘት ያስፈልገዋል:: ያኔ ኃጢአትን የሚያስጠላ ኃይል ያገኘዋል:: ጌታን እንዲያይ ጌታ ዓይኖቹን ይክፈትለት:: አሜን!

4ኛ/ ኃጢአት ማድረግ የአለማመናችን ምልክት ነው::

ቁ. 9 ና10 አንብብ:: የክርስቲያን ሕይወት ክርስቶስ ራሱ ነው:: የእግዚአብሔር ልጆች በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ስለሆኑ፣ እንደ ፍጥረታቸው መሄድና መኖር አለባቸው፣ 2ኛ ቆሮ. 5:17::

የዲያብሎስም ልጆች በፍጥረታቸው እንደ አባታቸው ዲያብሎስ ዓይነት አካሄድ ይሄዳሉ ማለት ነው፣ ዮሐ. 8:44፤ ኤፌ. 2:3:: የኃጢአት ልምድ ያለው እርሱ ከዲያብሎስ ወገን ነው:: ኃጢአትን ማድረግ ሊተው አይችልም::

ክርስቲያኖች እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ኃጢአትን መጥላት አለባቸው፣ ሮሜ 7:23-24:: የሚጠሉትም አዲስ ፍጥረት ስለሆኑ ነው:: መንፈስ ቅዱስም ኃይል ይሰጣቸዋል:: ወደ ኃጢአት ሳይሆን ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ማደግ አለባቸው፣ 2ኛ ጴጥ. 3:18:: እንግዲህ ወደ አሸናፊ ሕይወት እንደግ::

## ሸ) የፍቅር ሕይወት፣ 1ኛ ዮሐ. 3:11-24 አንብብ

በእነዚህ ቁጥሮች አገላለጽ፣ አንተ ክርስቲያን፣ የእግዚአብሔር ዓይነት ፍቅርና ሕይወት አለህ እንጂ ሙት አይደለህም:: ፍቅር የሚያሳየውን 5 ነገሮች ተከታትለን እንመልከት::

1ኛ/ ፍቅር፣ በሰዎች ዘንድ ያለውን ጥላቻና ክርስቲያኖች በሰዎች ዘንድ አለመወደዳቸውን ያሳየናል፣ ቁጥ. 11 ና 12 አንብብ::

ክርስቲያን ግን እርስ በርሱ መዋደድ አለበት:: እርስ በርሳችን የምንዋደደው ፍቅር ከእግዚአብሔር የመጣ ባሕርይ ስለሆነ፣ ይህን ባሕርይ አማኝ ከእግዚአብሔር ማግኘቱን ያሳያል:: ይህ የፍቅር ባሕርይ ከወዳጅነት ወይም ከስሜት የሚመጣ ዓይነት አይደለም:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ፍቅር በክርስቶስ በኩል የመጣ ነው:: ይህ ፍቅር የእግዚአብሔር ዓይነት ነው:: ይህ ፍቅር መንፈሳዊ ነው:: ከላይ የሚወርድ ነው:: ወደ ጌታ ከመምጣታችን በፊት የነበረን ፍቅር ምን እንደሚመስል በቁ. 12 ተመልከት:: የቃየን ዓይነት ነበረ:: እርሱም የውድቀትና የኃጢአት አባት፣ የጥላቻና የነፍስ ገዳይነት አባት ነው፣ ዘፍጥ. 4:1-16 ተመልከት::

2ኛ/ ፍቅር በዓለም ዘንድ ያለውን ጥላቻና አለመወደዳችንን ያሳያል

ቁ.13 ተመልከት:: ክርስቶስ በዓለም ዘንድ የተጠላ ነበረ፣ ዮሐ 15:18-20:: በእርሱ ላይ የደረሰ ሁሉ በክርስቲያንም ላይ ይደርሳል፤ ማቴ. 10:17 ና 22፤ ምዕ. 24:9 ተመልከት::

3ኛ/ ፍቅር እኛ በክርስቶስ ዘንድ መወደዳችንን ያሳያል::

ቁ.14 ና 15 አንብብ:: ክርስቲያን መሆንህ በምን ይታወቃል? መልሱ በፍቅር ነው:: እግዚአብሔር ልብህን ለውጦ ፍቅርን አልብሶሃል:: ፍቅር ከጸጋ ስጦታዎች ሁሉ በላይ ነው:: 1ኛ ቆሮንቶስ 13 አንብብ:: ፍቅር ለጌታ ብሎ ከመሞትም ይበልጣል::

4ኛ/ ፍቅር በእግዚአብሔር ዘንድ መወደዳችንን ያሳያል።

ቁ. 16 ና 17 እግዚአብሔር እንዲሁ ወዶናል፤ ዮሐ. 3:16። ክርስቶስ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአል፣ 1ኛ ዮሐ. 3:16። የእግዚአብሔር ፍቅር ልጁን አሳልፎ ለእኛ በመስጠት ሲታወቅ፣ የክርስቲያን ፍቅር ደግሞ ለሰው በመስጠት፣ ራስን አሳልፎ በመስጠት ይታወቃል። መስጠት የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው። ፍቅር መስጠትና መቀበል ብቻ ሳይሆን በመስጠት መጥገብና መርካትም ነው። ክርስቲያን ስስታም አይደለም።

5ኛ/ ፍቅር በእውነት ዘንድ ማን መሆናችንን ይገልጻል፤ ቁ.18-24

## የእውነት ዋሶች 3 ናቸው

1. በሥራ የሚገለጽ ፍቅር፤ ቁ. 18 አንብብ።

በቃል ብቻ ከመሆን ይልቅ ፍቅርን በሥራ እንገልጻለን። ክርስቲያን ፍቅርን በአፍ ብቻ ከሚገልጽ ይልቅ በልብና በተግባር ቢገልጽ ይሻላል።

መልካም ሥራ ደኅንነትን አያስገኝም። ደኅንነት በክርስቶስ በማመን ብቻ ይገኛል። በክርስቶስ የሚገኝ ደኅንነት ፍቅርን ያመጣል። የደኅንነት ኃይል ፍቅር ነው። የፍቅር ኃይል መልካም ሥራ መሥራት ሲሆን፣ መልካም ሥራ መሥራት የመንፈስ ፍሬ ነው።

2. የማይፈርድ ልብ፤ ቁ. 19-21 አንብብ።

ይህ ክፍል የውስጥ የልባችንን ምስክርነትን ያሳያል። የክርስቲያን ልብ ንጹሕ ነው፤ ማቴ. 5:8፤ መዝ. (24):4፤ መዝ. (51):10። ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን እውነትን ከሐሰት ለይቶ ማየትና መፍረድ ይችላል፤ መዝ. (36):9። ለራሳችን በልባችን ያለውንም ነገር ማየት እንችላለን። ታዲያ የልባችን ነገር ምን ይመስላል? ፍቅር በልባችን ካለ በስሜትና በአሳብ ብቻ ሆነን አንቀርም። ነገር ግን ከእውነትና ከሕይወት የሆነን ውጤት እናሳያለን። ይህም የልብ ዋስትናና የፍቅር ኃይል ነው። በውስጣችን ማለት

በልባችን ራስን የመውደድ ወይም አንድ ነገር የማግኘት ፍቅር ቢኖረን፣ ወይም በአንድ ኃጢአት ወድቀን ልባችን ቢከስሰን፣ እግዚአብሔር በዚያ ይፈርድብናል። ወዳጆች ሆይ፣ ልባችንስ ባይፈርድብን በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት አለን፤ ቁ. 21። እግዚአብሔር ከልባችን ይበልጣልና። ልባችን በሚፈርደው ነገር ንስሐ እንግባ። በመንፈስ ቅዱስና በፍቅር የልባችንን ጻድነት እንጠብቅ። እግዚአብሔር ፍቅርን ወደ ልባችን ያፈስሳል።

3. የጸሎት መልስ፤ ቁ 22-24 አንብብ

የጸሎታችን ኃይል በዓለም በምንኖረው ሕይወት ይታወቃል። በቃል ወይም በአንደበት ከመንበርከክ ይልቅ በተግባራችን በጉልበታችን ብንንበረከክ ይሻላል። እግዚአብሔር ጸሎት ወዳጆች ያድርገን። እግዚአብሔር ለለመናችሁት ሁሉ የጸሎት መልስ እሰጣለሁ ብሎ ዋስትና አልገባልንም። እንደ ፈቃዱ ግን ይሰጠናል፣ ቲቶ 3:4-7።

እምነትና ፍቅር ቢኖረን ትእዛዛቱንም ብንጠብቅ ጸሎታችን ተሰምቶ እንደ ፈቃዱ ይመልስልናል፣ 1ኛ ዮሐ. 5:14።

# ክፍል ሁለት

## ምዕራፍ 4 እና 5

## የእግዚአብሔር ልጆች በዓለም ፊት እንዴት መኖር እንደሚገባቸው ያስተምራሉ

### ሀ/ የማወቅና የመለየት ሕይወት፣ 1ኛ ዮሐ. 4:1-6 አንብብ

እውነትን ከውሸት ለይቶ ማወቅ ይቻላል ወይ? መልሱ አዎን ነው:: በእነዚህ ቁጥሮች የእውነት መንፈስና የውሸት መንፈስ ተለይቶ ይታወቃል ይላል:: ይህ የተጀመረው በኤድን ገነት መልካሙንና ክፉውን ለመለየት የሚያስችል ዛፍ በተበላ ቀን ነው፣ ዘፍጥ. 3:6:: ሰው በምድር ላይ ብዙ ዓይነት የምርመራ መሣሪያዎችን አግኝቶአል:: ነገር ግን ሰው በእነርሱ ተጠቅሞ እስካሁን ድረስ እግዚአብሔርን ሊያገኝ አልቻለም:: በተመሳሳይ መንገድ ሰይጣንም አይታይም:: ሰው ጥበበኛ ነኝ ሲል ሞኝ ሆነ፣ ሮሜ 1:22::

ሰው እግዚአብሔርን ሊያገኝ የሚችለው አስቀድሞ በእግዚአብሔር መንፈስ በመሞላት ነው:: በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል ብቻ እግዚአብሔርን ልናገኝ እንችላለን፣ 1ኛ ቆሮ. 2:9-15:: ስለዚህ እውነተኛውን መንፈስንና ሐሰተኛውን መንፈስን ለይቶ ሊያውቅ የሚችል በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራ ሰው ብቻ ነው:: ክርስቲያኖችም እግዚአብሔር በሰጣቸው መንፈስ እውነትን ከውሸት ለይተው የማወቅ ችሎታ ተሰጥቶአቸዋል::

ለመሆኑ እውነትን እንዴት ለይተን እናውቃለን? እውነትን ከሐሰት ለይተን እንድናውቅ በዚህ በምዕራፍ 4 ላይ 9 መመዘኛዎች ተሰጥተውናል:: 5ቱን በፊደል ለ ውስጥ ታገኛላችሁ::

1. በውስጣችን የሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንዲያድር ተሰጥቶናል:: ቁ. 1 አንብብ:: ምዕራፍ 3:24 ተመልከት:: የእግዚአብሔር መንፈስ በአማኞች ልብ እንደሚኖር ኢየሱስ

እንዲህ አለ፦ ዮሐ. 14:16፣ 17 ና 26፤ ምዕ. 15:26 አንብብ:: እርሱ የእውነት መንፈስ ተብሎአል:: ስለዚህ በቁ. 1 መንፈስን መርምሩ ብሎናል:: በአሁኑ ዘመን ብዙ የቤተ ክርስቲያን ዓይነት፣ የስብከት ዓይነት፣ የመጽሐፍና የትርጉም ብዛት፣ የሰባኪዎች ብዛትን ስንመለከት ይገርመናል:: የትኛው ልክ ነው? የትኛውስ ስሕተት ነው? ብለን እንጠይቅ ይሆናል:: በሐዋርያው ዮሐንስ ዘመንም ልክ እንደዚሁ ነበር:: ስለዚህ ነው እግዚአብሔር በዮሐንስ በኩል በመንፈስ ቅዱስ በኩል ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሰጠን::

መልሱ መንፈስን መረምሩ የሚል ነው:: ምክንያቱም ብዙ የሐሰት መምህራንና ሰባኪዎች፣ ነቢያት፣ እንዲሁም የሐሰት ቤተ ክርስቲያን ወደ ዓለም ገብተዋልና መርምሩ እያለ ለእኛ ማስጠንቀቂያ ይሰጠናል:: መቼም ቢሆን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት እውነት የሆነ ሁሉ እውነት ነው:: እንዲሁም ውሸት የሆነውም ውሸት ነው እንጂ ግማሽ ውሸት የሚባል ነገር የለም፤ ማቴ. 5:37::

በእግዚአብሔር ዘንድ ከቃሉ ውጭ የሆነ ሁሉ ውሸት ነው:: እውነት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በቃሉ ውስጥ ተጽፎ ይገኛል:: ስለዚህ የጽድቅ ጠላት ዲያብሎስ የጨለማ ገዢ ነው፤ 2ኛ ቆሮ. 10:4:: በአዳም ጊዜ በእግዚአብሔርና በአዳም መካከል በመግባት የእግዚአብሔርን ዓላማ ለማጥፋት ሞክሮ ነበር:: ዛሬም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ሐሰትን መዝራት ስለሚፈልግ መጠንቀቅ ይገባናል::

2ኛ/ በጌታ በኢየሱስ ታምነን በመመስከር ነው፤ ቁ. 2,3 አንብብ::

ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ዓለም እንደ መጣና ለኃጢአተኞች በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቶ ከሞት እንደ ተነሣና ወደ ሰማይ እንዳረገ፣ ለፍርድ ተመልሶ እንደሚመጣና እንዲሁም በስሙ ለሚያምኑት ደኅንነት መስጠት እንደሚችል፣ በእርሱ በማመን ብቻ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንደምንችል አምነን በምንመሰክር ሁሉ የእውነት መንፈስ ይኖራል:: ከዚህ እውነት ውጭና ከዚህ እውነት ሌላ ጨምሮ

የሚያስተምር ሁሉ ሐሰተኛ መንፈስ ነው፤ ራእይ 22:18-19:: ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውም አምላክም ሆኖ በሰው ላይ ሊፈርድና ሊያድን ባለ ሥልጣን መሆኑን የሚክድ መንፈስና ትምህርት ሁሉ ሐሰተኛ ነው::

አንባቢ ሆይ፣ አንተስ ክርስቶስን ማን ነው ብለህ ታምናለህ? 1ኛ ቆሮ. 12:3፤ ማቴ. 16:13-17::

ክርስቶስ በሥጋ ወደ ምድር መምጣቱን አውቆ ማመን ምን ይጠቅማል?

ብዙ ሐሰተኞች ጌታ እንደ ሰው፣ ሰው ብቻ ነው ይላሉ ወይም ጌታ አምላክ ብቻ ነው በማለት ይክዳሉ:: እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን ከሆነ፣ ጌታ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰውም ነው:: ሰውንና እግዚአብሔርን የሚያስታርቅ አማላጅ እርሱ ብቻ ነው፤ 1ኛ ጢሞ. 2:5፤ ገላ. 2:20፤ 1ኛ ዮሐ. 2:1-2::

የክርስትና ትምህርት ክርስቶስ አምላክ ሲሆን፣ የሰው ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር መምጣቱን ሲያረጋግጥ፣ እግዚአብሔር ወደ ሰው መምጣቱን እንጂ ሰው ወደ እግዚአብሔር በራሱ መቅረብ መቻሉን አያስተምርም:: ደግሞ በክርስቶስ በኩል ብቻ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንችላለን የሚል ነው፤ የሐዋ. ሥራ 4:12፤ ዮሐ. 14:6 አንብብ:: ሌላ መንገድ የለንም:: እውነትንና ሐሰትን ለይተን የምናውቅበት መለኪያው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው::

3ኛ/ በክርስቶስ አሸናፊዎች ስለሆንን፣ ቁ. 4

የእግዚአብሔር ሕይወት በእኛ ስለሚኖር ሐሰትንና እውነትን ለይተን በማወቅ ሐሰትን ማሸነፍ እንችላለን:: ክርስቶስ የሰውን ሕይወት ለመቅመስ ሥጋ ለብሶ በመምጣቱ፣ እኛም ከእርሱ በመወለድ ልጆቹ ሆንን:: የእግዚአብሔርን ሕይወት እንድንቀምስ ሆነናል:: እርሱ ዓለምን እንዳሸነፈ እኛም ዓለምን የማሸነፍ ኃይል ተሰጥቶናል:: ዛሬ በጌታ በመሆናችን ኅብረትን አግኝተናል:: እውነትና ሕይወትን ተቀብለናል:: ስለዚህ ሐሰትንና ክፉ መንፈስን ለማሸነፍ ኃይል መቀበላችንን እንመን:: በእናንተ

ያለው በዓለም ካለው ይበልጣልና ብሎአል፤ ሮሜ 8:31-37፤ ዮሐ.16:33::

4ኛ/ በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ልናውቅ እንችላለን

ቁ. 5 ና 6 አንብብ:: የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ቅዱስ በክርስቲያን ሕይወት ባለሥልጣን ነው:: እርሱ ይመራናል:: የእግዚአብሔር ቃል በእኛ ውስጥ ስለሚኖር እኛ የእርሱ ነን፤ ቃሉን እንሰማለን፤ እንታዘዛለን:: በዚህ ቦታ ሁለት ነገሮችን ያወዳድራል:: እነርሱም፣ ዓለም የሚናገረውን የዓለም ቃልና የእግዚአብሔር ቃል የሚናገረው ናቸው:: ከዓለም የሆኑት የዓለምን ቃል ይናገራሉ፣ ዓለምን ይሰማሉ፣ ይከተላሉም:: በአሁኑ ዘመን ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ጊዜ የላቸውም:: አምልኮ፣ ዝማሬ፣ ፈውስ ወዘተ... እንጂ ጥልቅ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል መልእክትን ለመስማት ጊዜ የላቸውም:: ቀስ በቀስ ከቃሉ እየራቁ ነው:: ቃሉን ለመማር አይፈልጉም፤ መሪዎችም አያስተምሩም ይሆናል:: ይህ አደገኛ ስለሆነ መጠንቀቅ አለብን:: ወደ ቃሉ እንመለስ:: የእግዚአብሔር የሆኑት ሁሉ ቃሉን ይሰማሉ:: ስለዚህ መለያ ምልክቱ የእግዚአብሔር እውነተኛ መንፈስ፣ እውነተኛ ጌታ፣ እውነተኛ የክርስትና ሕይወትና እውነተኛ ቃሉ ናቸው:: አንተስ አንባቢ ሆይ፣ በቃሉ ውስጥ ያለውን ሥልጣን ተረድተሃል?

## ለ/ እውነተኛ ሕይወት እንዳለ በፍቅር ይታወቃል፣

1ኛ ዮሐ. 4:7-21 አንብብ::

ሐሰተኛና እውነተኛን መንፈስ መለያ:-

1. ፍቅር ነው፤ ቁ. 7-16 አንብብ:: ፍቅር የአዲስ ፍጥረት ባሕርይ ነው:: በፍቅር ያልተገለጸ የመንፈስ አሠራር ሁሉ የሐሰተኛ ነው::

ቁጥር 7-16 እንደገና አንብብ:: ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን አሳየንና እናምናለን፣ የት ነው አረጋግጥልን ይላሉ::

ቁ.12 ላይ ማንም እግዚአብሔርን አላየም ይላል:: የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች እነ ሙሴ፣ ዘፀ. 33:16-23፣ ኢሳይያስ ምዕ. 6:1-9 እንዲሁም ሌሎችም እግዚአብሔርን እንደ አዩ አስመስሎ ይናገራል:: እግዚአብሔርን ማንም በሙሉ ክብሩ አይቶ አይድንም፣ ዘጸአት 33:20:: እነርሱም ቢሆኑ እግዚአብሔርን አላዩም:: የክብሩን ጨረፍታ አይተዋል እንጂ:: እግዚአብሔር ራሱን በልጁ በክርስቶስ ሊገልጽ ፈልጎ ክርስቶስን ሰጠ፤ ዕብ. 1:1-3:: ዛሬ ክርስቶስን በእምነት ያየ እግዚአብሔርን አይቶአል፣ ዮሐ. 14:8-10 ተመልከት:: ክርስቶስን በእምነት ዓይን ማየት ይቻላል:: በእምነት በክርስቶስ በኩል አድርገን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንችላለን:: ስለዚህ በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔርን በእምነት ማየት ይቻላል:: የክርስቶስ እምነት ወደ ልባችን ሲገባ ሕይወታችን በእውነተኛ ፍቅር ይሞላል:: ከዚያም እርስ በርሳችን መዋደድ እንጀምራለን:: እግዚአብሔርም በእኛ ውስጥ ይኖራል:: በእኛ መካከል የፍቅር ሕይወት ቢኖር፣ ሰው ሁሉ በእኛ አማካይነት እግዚአብሔርን ማየት ይችላል:: ፍቅር ባለበት እግዚአብሔር አለ:: እግዚአብሔርን በፍቅር አሳየው::

በተለይም የዓለም ሕዝብ ክርስቲያኖችን እንደ መጽሐፍ ስለሚያነቡ በፍቅራችን እግዚአብሔርን እናሳይ::

በቁ. 12 እና 13 ላይ ትልቅ ልዩነት አለ::

ቁ. 12 እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል ሲል፣ ቁ. 13 እኛም በእግዚአብሔር እንኖራለን ይላል::

ለዚህም ማረጋገጫ ከመንፈሱ ሰጥቶናል፤ ቁ. 14-16:: ሌላ ማረጋገጫ ደግሞ ቁ. 14-16 አንብብ:: እግዚአብሔር ልጁን የዓለም መድኃኒት አድርጎ ሰጥቶናል ይላል:: እግዚአብሔር እርሱን እንድናይ ልጁን ላከ፤ ልጁ ፍቅር ነው:: የእግዚአብሔር ፍቅር በልጁ በኩል ብቻ ነው የተገለጠው፣ ዮሐ. 3:16:: እኛም ሰውን ሁሉ መውደድ እንጀምራለን::

2ኛ/ <u>ፍቅር በፍርድ ቀን ድፍረትን ይሰጣል</u>፣ ቁ. 17

አንድ ትንሽ ልጅ ራቁቱን ቢሆን ወይም የተበጫጨቀ ልብስ ቢለብስ እንኳ አባቱ በሽንጉ ፊት ቢጠራው በድፍረት ወደ አባቱ ዘንድ እንደሚቀርብና ሳይፈራ ወደ አባቱ እንደሚጠጋ ሁሉ፣ ለክርስቲያን በፍርድ ቀን ድፍረት የሚሆነው ራሱ ያደረገውና የሠራው መልካም ሥራ ሳይሆን፣ ልጁ መሆኑ ነው:: ደግሞ ክርስቶስ ለእኛ ስላደረገልን መልካም ሥራ፣ እኛም በእምነት ስለ ተቀበልነው በፍርድ ዙፋን ፊት ለፍርድ ስንቆም ድፍረት ይሆንልናል፤ ሮሜ 8: 1፤ ሉቃስ 10:20:: የአማኝ ፍርድ በዚሁ ዓለም ክርስቶስን በተቀበለበት ጊዜ ተወግዶአል:: ነፃ ወጥቶአል፤ ዮሐ. 5:24፤ የክርስቲያን ስም አስቀድሞ በሕይወት መጽሐፍ ስለ ተጻፈ ክርስቶስ የእርሱን ፍርድ በዚሁ ዓለም ስለ ጨረሰለት ደስ ብሎት ድፍረት አግኝቶአል:: ምንም ኃጢአት እንደሌለበት ስለ ተቆጠረለት ድፍረት ተሰጥቶታል፤ መዝ. (32):1-2:: ክርስቶስ የእርሱን እፍረት ስለ ተሸከመለት ድፍረት ያገኛል:: በክርስቶስ ሞት የእግዚአብሔር ፍቅር በልቡ ስለ ፈሰሰ ድፍረት አግኝቶአል:: እርስ በርሱ እንዲዋደድ የፍቅር ሕይወት ስላገኘ በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንለታል:: እግዚአብሔርን አባ አባት ብሎ ይጠራል::

3ኛ/ <u>ፍቅር ፍርሃትን ያስወግዳል</u>፣ ቁ. 18 አንብብ

በእውነተኛ ክርስቲያን ልብ የፍርድ ፍርሃት ወይም የኩነኔ ፍርሃት አይኖርም:: በክርስቶስ በኩል ነፃ ስለወጣ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ይባርካል:: ክርስቶስ የእኛን እርግማንና የሞት ፍረሃትንም አስወግዶልናል፣ ገላ. 3:13::

ሀ)ፍርሃት የተወገደው በክርስቶስ ፍቅር ውስጥ ስለገባን ነው:: በእግዚአብሔር ፍርድ ቀን ያለ ፍርሃት ያለ ጭንቀት በፍቅር በፊቱ እንቆማለን:: የሚያቆመንም የእግዚአብሔር ጸጋ ነው፤ ኤፌ. 2:8-9::

ለ)ማንም ሰው ሊያየው የማይችለውን የእግዚአብሔርን ፊት ሳንፈራ በፍቅር ድፍረት ልናይ እንችላለን፣ ኢዮብ 19:27:: የክርስቶስ ሙሽራ ስለምንሆን በባልና ሚስት መካከል ፍርሃት እንደማይኖር ሁሉ፣ በክርስቶስና በእኛ ወይም በ<u>ሙሽራውና</u> <u>በሙሽራይቱ</u> መካከል ፍቅር ብቻ ይታያል፤ ራእይ 19:7-8::

4ኛ/ <u>በፍቅር ፍቅርን እንገልጻለን፣</u> ቁ. 19:20 አንብብ

እግዚአብሔር ፍቅር ነው፣ ቁ. 18:: እኛ እርስ በርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔርን ለዓለም ሁሉ እንገልጻለን:: እግዚአብሔርን ምን ያህል እንደምንወድደው ማረጋገጫው ወይም መለኪያው ፍቅር ነው:: ፍቅር ደግሞ ያየኸውን ሰው ምን ያህል ትወዳለህ? የሚል ነው:: ሰውን የምትወድደውን ያህል እግዚአብሔርን ትወድዳለህ ማለት ነው::

ሰው ስለ እግዚአብሔር ሲናገር ቀላል ነው:: ነገር ግን ስለ ሰው መናገር ከባድ ነው:: ምናልባት እግዚአብሔርን እወደዋለሁ፤ ሰው ምን ያደርግልኛል ትል ይሆናል:: ሰው ራሱን ወድዶ የሰውነቱን አንድ ክፍል ሊጠላ እንዴት ይችላል? እንደዚሁም ሰው እግዚአብሔርን ወድዶ ሰውን ሊጠላ እንዴት ይችላል? አይሆንም:: እንግዲህ እግዚአብሔርን ከወደድን ሰውንም መውደድ አለብን:: 1) በመጸለይ 2) በመርዳት 3) በመጠጋትና ወንጌልን በመናገር ከገሃነም እሳት እንዲድኑ ፍቅራችንን እንግለጽ:: ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር የለም::

5ኛ/ <u>የእግዚአብሔር ትእዛዝ በፍቅር ይፈጸማል፣</u> ቁ. 21

በዚህ ቁጥር መሠረት ከሰዎች ጋር ትክክል በምንሆንበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ደግሞ ትክክል እንሆናለን:: ሰውን ስንወድ እግዚአብሔርንም እንወዳለን ማለት ነው:: ሰውን ስንጠላ እግዚአብሔርንም መጥላት ጀምረናል ማለት ነው:: እንግዲህ ሰውን እንውደድ፣ መልካምንም እናድርግለት::

እውነተኛ ፍቅር እግዚአብሔር ነው:: እውነተኛ ፍቅር ከእግዚአብሔር ነው:: እውነተኛ ፍቅር ወደ ልባችን ከገባ ሰውን እንድንወድ ያደርገናል:: ሰውን የምንወድ ከሆነ፣ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያደርሰው መንገድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ እንመሰክራለን:: ከሰይጣንና ከሞት ነፃ የሚወጡበትን መንገድ እንምራቸው፣ ዮሐ. 14:6፤ ማቴ. 7:13-14፤ ሕዝ. 33:11::

## ሐ) አሸናፊና ሕያው የሆነ የክርስቲያን ሕይወት፣ 1ኛ ዮሐ. 5፡1-12

ክርስቲያን ሆይ፣ ክፉውን እያሸነፍህ ነውን?

በዮሐንስ መልእክት ምዕራፍ 5 ላይ 6 ጊዜ ማሸነፍ የተባለ ቃል ተጽፎአል። እንደዚሁም በዮሐንስ ራእይ 12 ጊዜ ስለ ማሸነፍ ወይም ድል መንሣት ተጽፎ ስለምናገኝ፣ እነዚህን መጽሐፎች የጻፈ ዮሐንስ ስሙ አሸናፊ ነው ብንል አያሳፍረንም። ሕይወት ማሸነፍ የሌለውን ሕይወት አለ ለማለት አያስደፍርም። ሕይወት ያለው ብዙ ነገሮችን ያሸንፋል። አንተም ሕይወት ስላለህ በሽታን፣ ብቸኝነትን፣ ድህነትን፣ ብርድን፣ ረሃብን፣ ወዘተ... አሸንፈሃል። ለማሸነፍ ትግል ያስፈልጋል። ከዚህ ቀጥሎ አንድ ምሳሌ ተመልከት፡- በልጅነቴ እረኛ ነበርኩ። እረኞች የእያንዳንዱ መንደር ልጆች የራሳቸው የሆነ ቡድን አላቸው። በየጊዜው የአንዱ መንደር ልጆች ከሌላ ራቅ ካለ መንደር ልጆች ጋር ትግል ይገጥማሉ። አንዳንድ ጊዜ ነፃ ትግል ሲሆን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የጥልና የድብድብ ይሆናል። አንድ ወቅት ከእኛ ሌላ በጣም ጠንካራ የሆነ ቡድን ነበረ። በዚያ ቡድን ጉልበተኛ የሆኑ ሁለት ልጆች ስማቸው ገበየሁና ሲዴ የተባሉ ነበሩ። የእነርሱ ቡድን ከብቶቹን ይዞ ሲመጣ የእኛ ቡድን ስለሚፈራው ከሩቅ እንሸሽ ነበር። አንድ ቀን ግን እንዲህ ሆነ፣ ያ ኃይለኛ ቡድን ሳናውቅ በድንገት ከበበንና ያዘን። ብንሸሽ የዘላለም መሳቂያና መሰደድ ከዚያም ባሪያዎች መሆናችንን አውቀን ቆመን ቀረን። እነርሱም ቀረቡና በሉ ኑ አሁን ትግል እንግጠም እኛ ሲዴን ሰጥተናል። ከእናንተም አንድ ልጅ ስጡን አሉ። እኛ ግን በተለይ ሲዴ ጉልበተኛ ስለሆነ እጅግ ፈራን። በተለይ እኔ በልጅነቴ በጣም ፈሪ ነበርኩ። ሲዴም በመካከላችን ቆሞ ልብሱን አወለቀና ራቁቱን ሆኖ ወንድ የሆነ ይምጣ አለ። በዚያን ጊዜ ሁላችንም ፈራን። በተለይ እኔ በጣም ፈራሁ። ሲዴም ወደ እኛ ቡድን ተመለከተና አንተን እፈልግሃለሁ ብሎ እኔን ጠራኝ። ጉልበት ባይኖረኝም በቁመት ከእኛ ቡድን ልጆች ረጅም ሆኜ በመገኘቴ ነበር። የእኛ ቡድን ልጆችም ፈርተው ሂድና ግጠመው አሉኝ። እኔም በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ልብሴን ወደዚያ ጣልኩና ከሲዴ ጋር ትግል ገጠምን። ሲዴን በደረቴ ብድግ

አድርጌ አንጠለጠልኩና ከመሬት ወደ ላይ አነሣሁት። ሲዱ አጭር ስለ ነበረ እግሮቹ በአየር ላይ ተንፈራፈረ። እኔም ከፍርሃት የተነሣ ሲዱን በደረቅ መሬት ላይ ወደ ታች ወረወርኩት። ሲዱን የደረቀው መሬት ራሱን መትቶት ስለነበረ ጩኸቱን ለቀቀው።

ያ ኃይለኛ የተባለው ቡድን ሲዱን ይዞ ወደ ቤት ሸሽታቸውን ቀጠሉ። ከዚያን ቀን ጀምሮ ወደ እኛ ቡድን አይቀርቡም ነበር። እኛም ከዚያ ቀን ጀምሮ አሸናፊዎች ሆነን ቀረን።

ክርስቲያን ሆይ፣ ከጠላት ጋር ካልታገልን በስተቀር አሸናፊ ወይም ተሸናፊ መሆናችን አይታወቅም። እግዚአብሔር ለአሸናፊነት ጠርቶናል። አንተንስ የሚያስቸግርህ ጠላት የትኛው እንደሆነ ታውቃለህ? ለምሳሌ፣ ቁጣ ነው? ንዴት ነው? ቂም መያዝ ነው ሥርቆት ነው? የትኛው ይሆን? ግጠመውና በእግዚአብሔር ኃይል ማሸነፍ ትችላለህ። ቀጥሎ ያሉትን ጥቅሶች ተከታተል።

1ኛ/ አሸናፊ ሕይወት በፍቅር ይገኛል፤ ቁ. 1-3 አንብብ

የሚወድ እያለ እንደገና ለ14ኛ ጊዜ ስለ ፍቅር ይናገራል። ፍቅር ከሁሉ ነገር በላይ አሸናፊ ነው። ፍቅር ያለው ሰው ምንጊዜም ቢሆን አሸናፊ ነው።

የዮሐንስ መልእክት በተጻፈበት ዘመን የሮም ንጉሥ ኔሮ ክርስቲያኖችን በመግደልና በማሳደድ ላይ ነበር። ከዚያም በላይ የኢየሩሳሌምን ከተማ አፍርሶና አቃጥሎ ስለነበረ ክርስቲያኖች በታላቅ መከራና ስደት ውስጥ ነበሩ። በዚህ ወቅት የእግዚአብሔር መልእክት <u>አሸንፋችኋል፣</u> በእምነታችሁ ድል <u>አድርጋችኋል</u> የሚል ነበር። የሮም መንግሥት ጥላቻን አስተማረ። ክርስቶስ ግን ፍቅርን አስተማረ። የሮም መንግሥት በኃይልና በጦርነት አሸነፈ። ክርስቶስ ግን በፍቅር አሸነፈ። የሮም መንግሥት በመግደል ሊያሸንፍ ሞከረ። ክርስቶስ ግን በመስቀል ላይ በመሞት ድል አደረገ። የክርስቶስ መሣሪያ ለዚህ ዓለም ልዩና አዲስ ዓይነት መሣሪያ ነበረ። ያውም ፍቅር ነው፤ ምዕ. 3፡1 ና6።

ክርስቶስ ከእግዚአብሔር እንደ ተወለደ የሚያምን ሁሉ አሸናፊ ነው። እንዲሁም ክርስቶስ ሰውና አምላክ እንደሆነ፣ ክርስቶስ በሥጋ መጥቶ በመሞት ለእኛ ሕይወት እንደ ሰጠ የሚያምን ሁሉ እርሱ አሸናፊ ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ ያለው ሁሉ የእግዚአብሔር ፍቅር አለው። ፍቅር ያለው ሁልጊዜም ያሸንፋል።

2ኛ/ አሸናፊ እምነት፣ ቁ. 4 ና5 አንብብ

በክርስቶስ ላይ እምነት ያለው ሰው አሸናፊ ነው። ሰይጣንን ያሸንፋል። ዓለምንና ሥጋን ያሸንፋል። ለምሳሌ፣ የሲጋራን ሱስ፣ የጫትንና የሐሽሽን ልማዶች ያሸንፋል። የዳንስ ክበብንና የሲኒማ፣ የክፉ ጓደኞችን አሳብና ምክሮች ያሸንፋል፤ ምሳሌ 4:14-19 አንብብ።

የማሸነፍ ኃይልና ምሥጢር ምንድን ነው? መልሱ:-

1. በጌታ ዳግም መወለድ ነው፤ ዮሐ. 3:3-5፤ 2ኛ ቆሮ. 5:17።
2. ከጌታ የምንቀበለው መንፈስ ነው፣ እምነት ነው፣ ሮሜ 8:9-11። ዳግም ከጌታ ያልተወለደና እምነት የሌለው ክፉን የማሸነፍ ኃይል የለውም። የድል አድራጊነት ኃይል እንዲሰጥህ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ መወለድና እምነት ማግኘት አለብህ። ወደ ጌታ ዛሬውኑ ና።

አንባቢ ሆይ፣ እግዚአብሔር በእኔ አድሮ የማሸነፍን ሥራ እንዲሠራ ካልፈቀድኩለት በስተቀር እግዚአብሔር እኔን አስገድዶ ምንም መሥራት አይችልም። በእኔ ሕይወት ውስጥ ክርስቶስ እንዲገባ ከፈቀድሁ፣ እኔና እግዚአብሔር አብረን በእኔ ሕይወት ትልቅ ሥራ መሥራት እንችላለን። የአሸናፊነትን ሕይወት መኖር እችላለሁ። አሸናፊነት ያለውን ሥራ መሥራት እችላለሁ፤ ፊልጵ. 4:13። እኔ ካልፈቀድኩ እግዚአብሔር በእኔ ሕይወት ምንም መሥራት አይችልም። እኔም ለብቻዬ አሸናፊ ሕይወት ሊኖረኝ አይችልም፤ ዮሐ. 15:5-11።

በዚህ መልእክት በቁ. 4 እና 5 ላይ ጸሐፊው 3 ጊዜ ያህል ዓለምን ማሸነፍ እያለ ይናገራል። ዓለም ምንድን ነው? ዓለምንስ እንዴት ማሸነፍ እንችላለን? ዓለምን በሁለት ቦታ ከፍለን

እንመለከታለን:: እነርሱም:- ውጫዊ ዓለምና ውስጣዊ ዓለም ናቸው:: ዓለም ሲል ምድርን አይደለም::

1ኛ/ ውጫዊ ዓለም:- ይህ ዓለም ከእኛ ውጭ በሰይጣንና በተከታዮቹ የሚመጣ ዓለም ነው:: ይህ ውጫዊ ዓለም ክርስቲያን ሊለቀቅ ወይም ነፃ ሊወጣ የሚችልበት ዓለም ነው:: ለምሳሌ፣ ከውጭ ሊመጣ የሚችል እንደ ተንኮል፣ ጥላቻ፣ ስድብ፣ ሐሜት፣ ስደት፣ ወዘተ... ያሉ ናቸው:: ይህን ዓለም መጽሐፍ ቅዱስ የዓለም ሥራዎች ብሎ አስቀምጦአል፤ ገላ. 5:19-21:: እነዚህንና ሌላም የመሳሰሉትን መጽሐፍ ቅዱስ የሥጋ ሥራ ብሎ አስቀምጦአቸዋል:: ይህ ዓለም ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ፣ ከአገር የሚያፈናቅል ዓለም ነው:: ክርስቶስንና ወገኖቹን መጥላት ዋና ተግባሩ ሲሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ለሐዋርያት ከዓለም ምን መጠበቅ እንደሚገባቸው ተናግሮአል፣ ዮሐ. 15:18-19፤ ዮሐ. 16:33 ተመልከት:: ክርስቲያን ይህን የመሰለ ውጫዊ ዓለምን ማሸነፍ ይችላል:: ይህን ዓለም የማሸነፍ ኃይል ክርስቶስ ራሱ ነው:: እርሱን መልበስ አለብን፤ ሮሜ 13:11-14:: እርሱ በእኛ ሕይወት እንዲገባ ከፈቀድን (ራእይ 3:20) ድል እናደርጋለን፣ ፊልጵ. 4:13::

2ኛ/ ውስጣዊ ዓለም:- ሌላ የሚዋጋን ጠላት ውስጣዊ ዓለም ነው:: ይህ ውስጣዊ ዓለም ልንለቅቀው የማንችለው ዓለም ነው:: ይህም ለምሳሌ ሥጋችን፣ ኑሮአችን ወይም አሮጌ ፍጥረታችን ነው:: ከእነዚህ ከሁለቱ ዓለማት የትኛው ከፉና አደገኛ ነው? ብትሉ፣ አደገኛው ውስጣዊው ዓለም ነው:: ክርስቶስ በማርቆስ 7:20-23 ላይ እንዲህ ብሎአል፣ የውጭን ጠላት ማሸነፍ ቀላል ነው:: የውስጥን ጠላት ማሸነፍ ግን ከባድ ነው:: ሮሜ 7:18-20 ሐዋርያው ጳውሎስ ሁለት ዓይነት ዓለም በውስጡ እንዳለ ገላ. 6:14 ቢናገርም፣ እንኳ አሸናፊው እምነታችን ነው አለ:: የክርስቶስ የመስቀሉ ኃይል የውስጡንም የውጭንም ዓለም ኃይል ስለተቆጣጠረውና ስላደከመው አሸናፊዎች እኛ ነን:: ከአሸናፊዎ ችም በላይ እንበልጣለን፣ ሮሜ 8:37::

3ኛ/ አሸናፊ ክርስቶስና ምስክርነቱ፣ ቁ. 6-12 አንብብ

ኢየሱስ ክርስቶስ አሸናፊ ስለሆነ የአሸናፊ ክርስቲያኖች ሕይወት ከእርሱ ጋር የተጣበቀ ነው። ክርስቲያን ማንን ይመስላል ብትሉ አለቃውን ይመስላል። ክርስቲያን ማን መሆኑን በሕይወቱ ኖሮ ያሳያል። የክርስቲያን ሕይወት ትልቅ ምስክርነት አለው። ክርስቶስ እንዳሸነፈ ሁሉ እኛም ማሸነፍ እንችላን።

1. ክርስቶስና ምስክሮቹ፣ ቁ. 6-9 አንብብ

ቁ. 6 ውኃና ደም። ውኃ የክርስቶስ ሕይወት ምሳሌ ነው።

ውኃ ጥምቀትንና መንፈስን በሕይወቱ የፈጸማቸውን ጽድቅን ሲያሳይ ደሙ ለደኅንነታችን የፈሰሰ የክርስቶስ ደምና ሞቱ አስፈላጊ እንደሆነ ያመለክታል። ከጐኑ የፈሰሰው ደም ምስክር ነው፣ ዮሐ. 19:33-35። በደሙ ጠላትን ይመታል፣ ራእይ 12:11። ክርስቲያን ድል ያገኛል። ለደኅንነታችን የክርስቶስ አምላክ መሆንና ሰው መሆን በጣም ተፈላጊ ነው። አምላክ በመሆኑ የአምላክነትን ሥራ ሲሠራ፣ ሰው በመሆኑም የእኛን የሰዎችን ችግር ቀምሶአል፣ ሞቶአል። ስለዚህ ክርስቶስ አንድ ሳይሆን ሁለቱም ባሕርይ አለውና የአምላክንና የሰውን መለኪያ ሚዛን የሞላ እርሱ ብቻ ነው። የክርስቶስ ደም ትልቅ ኃይል አለው። አንድ አዝማች እንዲህ ይላል:-

ግሩም ኃይል ኃይል አለው በደሙ
በክቡር በጉ ደም
ኃይል አለው ግሩም ሥራ የሚሠራ
በከበረው በኢየሱስ ደም።

አንባቢ ሆይ፣ አንተስ የክርስቶስ ደም ኃይል እንዳለው ታምናለህ? በእርሱ ደም ልትፈወስ በጌታ እመን። የክርስቶስ ደም ስለ እግዚአብሔር ምስክርነት የሚሰጥ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌላም ምስክሮችም አሉት። እነርሱንም በቁ. 7 ላይ አንብብ። በሰማይ ያለው ምስክር ነው፣ በሰማይ ያለው መንፈስ ነው። እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ ዮሐ. 4:24። ወይም ሥላሴ ስለ ክርስቶስ ምስክር ነው።

አብ መሰከረ፣ ማቴ. 3:17፣ ማቴ. 17:5 ተመልከት::
መንፈስ ቅዱስ፣ ዮሐ. 15:26 ተመልከት::
ቃሉ ወይም ወልድ ዮሐ. 14:1
ሁሉም እውነትን መሰከሩ:: ምስክርነታቸው እውነተኛ ነው፣ ዮሐ. 8:17-18፤ ምዕ. 5:37:: ደግሞ የክርስቶስ ሥራ ራሱ ምስክር ነው:: ሲሠራ የነበረው የእግዚአብሔርን ሥራ ነበረ፣ ዮሐ. 14:11፤ ዮሐ. 10:38:: ዛሬም በምድር ላይ እግዚአብሔር በክርስቶስ ስምና ደም ተአምር እየሠራ ነው::

ቁ. 8 አንብብ:: ዛሬ በምድር የሚመሰክሩትን ተመልከት:: መንፈስ፣ ውኃ፣ ደም ይላል:: በሰማይ ያለው ምስክር አንድ እንደሆነ፣ እንዲሁም በምድር ያለው ምስክር አንድ ሆነው ይስማማሉ:: በሰማይ ሆነ በምድር ያሉት ምስክሮች አንድ ሆነው የሚመሰክሩት ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ዓለም እንዲያውቅና እንዲቀበለው ነው:: ዓለም ግን አላወቀውም፤ ዮሐ. 1:9-12:: እነዚህ ምስክሮች ስለ ክርስቶስ አምላክነትና አዳኝነት እንዲህ ብለው መስክረዋል:-

1. መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ ልደት መልአክ ለማርያም የምሥራችን ባበሰረ ጊዜ፣ ሉቃስ 1:35፤ ዕብ. 3:7 ተመልከት::
2. ውኃ ስለ ክርስቶስ አምላክነት በጌታ ጥምቀት መሰከረ፣ ማቴ. 3:16 ና 17 በመስቀል ላይ ዮሐ. 19:33-35 መሰከረ::
3. ደም፣ ስለ ክርስቶስ ሞትና መሥዋዕትነት፣ ዮሐ. 19:34-35::

ኢየሱስ በሞቱ ተፈጸመ አለ፤ ዮሐ. 19:28:: በሰማይና በምድር ያሉት ምስክሮች ክርስቶስ አምላክና ሰው መሆኑን ሲመሰክሩ የእርሱን ሥራ ይመሰክሩ ነበር ፣ ዮሐ. 8:17 ና 18፤ የሐዋ. 5:32::

የሰው ምስክር ስለ መቀበል፣ ቁ. 9

የሰው ምስክር በፍርድ ቤት ደረጃ የሚያስፈልግ ከሆነ በተለይም የእውነተኛ ሰዎች ምስክርነት ማመን ከቻልን በመጽሐፍ ቅዱስ ያሉት ታማኝ እውነተኛ ምስክሮችን መቀበል

እንዴት ያቅተናል? በተለይም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነትና መሪነት መጽሐፍ ቅዱስን እንዲጽፉ የተደረገላቸውን 40 የሚሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችንና ምስክርነታቸውን መቀበል አለብን:: እነዚህ 40 የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ይመሰክራሉ? መልሱ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና አዳኝ መሆኑን ይመሰክራሉ፣ ፊልጵ. 2:11:: ለእርሱ ስገዱለት ይላሉ:: ከዚህ ሁሉ በላይ የሰውን ምስክር በምድር የምንቀበል ከሆነ፣ ከሰማይ የሚመሰክረውን የእግዚአብሔርን ምስክርነት ለምን አንቀበልም?

የእግዚአብሔር ምስክር በቂና አጥጋቢ ነው:: ክርስቶስን የምንቀበለው እግዚአብሔርና ሰው ስለ መሰከሩለት ነው:: የእግዚአብሔር ምስክር ከሁሉ ይበልጣል:: ስለ ልጁ የመሰከረውን ምስክርነት ባንቀበል እምቢተኞችና ወንጀለኞች እንሆናለን:: ማምለጫ አይኖረንም፤ ዕብ. 2:3፤ 10:28-31::

2. <u>ክርስቲያኖችና ምስክርነታቸው</u>፣ ቁ. 10-12 አንብብ

በእነዚህ ጥቅሶች መሠረት ክርስቲያኖች ምን እንደምናምን ብቻ ማወቅ በቂ አይደለም:: ነገር ግን ለምን እንደምናምን ማወቅም አስፈላጊ ነው:: በልጁ የሚያምን በነፍሱ ምስክር አለው ሲል፣ ስሜት ማለት አይደለም ወይም ማስመሰል ማለት አይደለም፤ ይሆናል ብሎ ማሰብም አይደለም:: ነገር ግን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው የመዳን እርግጠኝነትን ማግኘት ማለት ነው:: የዘላለም ሕይወት ማግኘታችንን በነፍሳችን ማረጋገጥ እንችላለን ማለት ነው:: እንደዚህ ካልሆነ እግዚአብሔርን ውሸተኛ ማድረጋችን ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔር ስለ ልጁ የገለጸውን ምስክርነት መቀበል ወይም መጥላት የእኛ ፋንታ ነው::

ቁ. 12 ላይ እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወትን እንደ ሰጠን፣ ያም ሕይወት በልጁ በኩል ብቻ መሆኑን ገልጸአል:: ስለ ክርስቶስ የሚመሰክሩት:- አብ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ የራሱ ሥራ ፣ ዮሐ. 5:36 ነው:: ፍጥረትና ታሪክ የሐዋ. ሥራ 14:17 ሰዎችም ናቸው::

መ/ <u>የዘላለም ሕይወት ዋስትና፣</u> 1ኛ ዮሐ. 5:13-21 አንብብ።

በዚህ በ1ኛ ዮሐንስ 5:13-21 ባለው በመጨረሻ ቁጥሮች አማካይነት የዘላለም ሕይወት ዋስትና ወይም እርግጠኝነት ይሰጣል። ለዚህ ተጠራጣሪ ዓለም ወይም ሕዝብ በዐመፅ ሕይወታቸው የዘላለም ሕይወትን ለሚከላከሉት (ሮሜ 1:18)፣ በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወት መኖሩን ያረጋግጥላቸዋል። ለደኅንነት መሠረት በጌታ ማመን መሆኑን ሲገልጽ፣ እምነት አንድን ነገር ማመን ወይም በእርሱ መኖር እንደሆነ ያመለክታል፣ ዕብ. 11:1። ያውም በሥጋዊ ዓይን የማይታየውን እግዚአብሔርን በመንፈሳዊ ዓይን በማመን ማየትና በእርሱ ተስፋ መቆም ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ጸንቶ መቆም ነው። እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ሮሜ 10:17።

ዓለም የተጠራጠረበት ምክንያት ምንድን ነው? ይህች ዘመናዊ ዓለማችን በስሜት፣ በፍልስፍና፣ በራሷ ጥበብ እንዲሁም በሃይማኖት ተወጥራለች። ከዚህም የተነሣ በመጠራጠር አዘቅት ውስጥ ገብታለች። እንደዚህ ላለች ዓለም እምነትንና በክርስቶስ እምነት በኩል ያለውን የዘላለም ሕይወት ዋስትና ማቅረብ ይገባናል። በእምነት የመዳን እርግጠኝነት ይገኛል ብለን እንመሰክራለን።

በዚህ መልእክት ውስጥ 7 ጊዜ «እናውቃለን» እያለ በእምነት መዳናችንን ያረጋግጥልናል። አንባቢ ሆይ፣ አንተስ እምነት አለህ? በጌታ በማመን ደኅንነት እንደሚገኝ አረጋግጠሃል ወይ?

ዮሐንስ ራሱ አውቆ እኛም እንድናውቅ ጽፎልናል። በእምነት ለመዳን ተስፋ አለኝ አይልም። የምድንም ይመስለኛል አይልም። እንደምድን ይሰማኛልም አይልም። ነገር ግን ቀምሶ እንዳወቀ አድርጎ እርግጠኛ ነኝ፤ የዘላለም ሕይወት አለኝ፣ አግኝቼዋለሁ፣ በእኔ ውስጥ ገብቶአል፤ በነፍሴ ውስጥ ታትሞአል ይላል። እምነት የጋለ ስሜት ብቻ አይደለም ይላል።

ስለዚህ እምነት ከውስጥ የመነጨ ነው:: እምነት የገዛ ነፍስንና አእምሮን የሚገዛ ነው:: ወደ እውነተኛ የአእምሮ አሳብ የሚያመጣ ነው:: እምነት እውር አይደለም:: እምነት የሌለው ግን እውር ነው፣ 2ኛ ቆሮ. 4:4:: ከልብ እውርነት የሚያድነን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው::

በ1ኛ ዮሐንስ 5:13-21 ድረስ ለዚህ ለተጠራጣሪ ዓለማችን የምናቀርባቸው 4 ነገሮች አሉ::

1ኛ/ <u>የዘላለም ሕይወት አቋም ዋስትና ነው</u>፣ ቁ. 13 ተመልከት::

ለዚህ ለተጠራጣሪ ዓለማችን የምንገልጸው ነገር፣ መጀመሪያ ምን እንዳመንንና ለምን እንደምናምን ነው:: የምናምነው በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እምነታችንን የሚገልጹ ሁለት ነገሮች አሉ:: እነዚህም:- የሚታዩና የማይታዩ ነገሮች ናቸው:: ወይም ውስጣዊና ውጫዊ ነገሮች ናቸው::

1. <u>ውስጣዊ</u> ማለት ለሰው የማይታይ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው የውስጥ ለውጥና አሠራሩ ነው:: ለመንፈሳችንና ለልባችን መንፈስ ቅዱስ ይመሰክርልናል:: በእግዚአብሔር ልጅ በማመን የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ ይለናል፣ ሮሜ 8:13:: የውስጥ ጤንነት አለን ማለት ነው:: የውስጥ እረፍት አለኝ ማለት፣ የውስጥ ፍርሃት፣ ሥቃይና ጭንቀት ሁሉ ቀርቶ አእምሮዬ ስላረፈ ያለ ሥጋት እሄዳለሁ፣ እተኛለሁ:: ከሞት በኋላ ያለው ተስፋ ብሩህ ሆኖልኛል:: ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር ስለአገኘሁ፣ ከሰውና ከፍጥረት ሁሉ ጋር ሰላም አለኝ ማለት ነው::
2. <u>ውጫዊ</u> ማለት ለሰው የሚታይ የተለወጠ ሕይወት ማለት ሲሆን፣ ለምሳሌ የሰውነት ጤንነት ማግኘትና የሕይወት ዋስትና ነው:: ሰላማዊ መሆን፣ ሰውን መውደድ፣ ደስተኛ መሆን፣ እንዲሁም ለሰው ትክክለኛ ነገር ማድረግ፣ ከኃጢአት ልማዶች መራቅ ውጫዊ ለውጦች ናቸው:: ስለዚህ ለዓለም የምናወራው መልካም ዜና አለን:: ይህ የዘላለም ሕይወት ዋስትና ቅምሻ ነው:: እንግዲህ ክርስቲያኖች በምድር የሕይወት ዋስትና ተጠቃሚዎች

ስለሆኑ፣ ከዚህ የተነሣ ለዓለም የሚገልጹት 5 ነገሮች አሏቸው::

ሀ) የኃጢአት ዕዳ ጥያቄ ተፈጽሞልናል፣ሮሜ 8:1፤ 1ኛ ዮሐ. 1:7-10:: አንድ ሰው ከባድ የገንዘብ ዕዳ ቢኖርበት እስካልተከፈለ ድረስ ነፃ መሆን አይችልም:: ምናልባት በአሳቡ ስለ ዕዳ አላስብም ልርሳው ቢል እንኳን ዕዳው ካልተከፈለ ነፃ አይሆንም:: ልክ እንደዚሁ የኃጢአት ዕዳ በሰው ላይ ይኖራል:: የኃጢአታችንን ዕዳ ክርስቶስ ከፍሎአል:: ያንን በእምነት መቀበልና እርሱን መማጸን ያስፈልጋል:: ለሚያምኑት የኃጢአት ዕዳ በክርስቶስ ደም ተከፍሎ ተፈጽሞአል:: እግዚአብሔርም በእምነት በክርስቶስ ውስጥ አይቶን ኃጢአታችንን ይቅር ብሎናል:: ስለዚህ እግዚአብሔር የታመነ አምላክ ስለሆነ አጽድቆናል:: ዕዳችን ስለተከፈለ ነፃ ሆነናል ብለን እናወራለን፣ 1ኛ ዮሐ. 2:12::

ለ) የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ችለናል፤ 1ኛ ዮሐ. 2:4-5:: ይህ የሆነው ውስጣችን በአዲስ ልደት ስለተለወጠ ነው፤ 2ኛ ቆሮ. 5:17፤ ሕዝ. 37:26-27፤ ኤር. 31:31-34፤ ቲቶ 3:4-7 ተመልከቱ::

ሐ) ሰውን እንወዳለን (እናፈቅራለን) 1ኛ ዮሐ. 3:14:: ፍቅር ስለ ሕይወት ይመሰክራል:: ፍቅር እውነተኛ ሥራ ይሠራል፤ ዮሐ. 13:34-35:: ፍቅር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነው:: ፍቅር በአማኞች ልብ ውስጥ ሊኖር ያስፈልጋል::

መ)የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት በውስጣችን አለን፣ 1ኛ ዮሐ. 3:24:: መንፈስ ቅዱስ ለሕይወታችን ይመሰክራል:: እኛ ራሳችን የተለወጠ ሕይወት መኖራችንን እንረዳለን:: ሌሎች ሰዎችም ይረዳሉ፣ ይመሰክራሉ::

ሠ) የእግዚአብሔር ቃል (ትእዛዝ) በእኛ ውስጥ ይኖራል፣ 1ኛ ዮሐ. 5:2-3:: የእግዚአብሔርን ቃል መጽሐፍ ቅዱስን እንታዘዛለን፤ ሕጉንም እንፈጽማለን:: በዚህ መንገድ

በክርስቶስ የዘላለም ሕይወት አለ ብለን ለዓለም እናወራለን፣ እንገልጻለን።

2ኛ/ <u>የጸሎት ኃይል ዋስትና ነው፤</u> ቁ. 14-15 አንብብ

ይህ ክፍል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት የጸሎት ክፍሎች አንዱ ነው። ከጸሎት ክፍሎች መካከል በጣም የተለመደ ክፍል ነው። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሦስት የጸሎት ቁም ነገሮችን እንመለከታለን።

1. ጸሎት ማለት ለአምልኮ ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብና መጠጋት ነው። ጸሎት ማለት ምናልባት ይሆን ይሆን ማለት ሳይሆን፣ በእርግጥ መንፈሳዊ ሕይወትን ከመንፈሳዊ አባት ከእግዚአብሔር ጋር ማገናኘት ነው። በመንፈሳዊ አባት ባሕርይ ውስጥ መግባት ነው። በእርሱ ፊት በድፍረት ቀርቦ ማነጋገር፣ ልመና ቢሆን ወይም ምስጋና ቢሆን ወይም ምልጃ ቢሆን ማቅረብ ማለት ነው። ደግሞም እርሱ የሚለውን መስማት ነው። የምናምነውን ካወቅን ወደ እርሱ ለመጸለይ እንችላለን። ሰማያዊ አባታችንን በእርግጥ ካወቅን የጸለይነውን እንደሚያደርግልን በእርግጥ እናምናለን። እንደ ፈቃዱም ከጸለይን መልስ እናገኛለን። በድፍረት በነፃ ለመነጋገርና አሳባችንን በእርሱ ፊት ለማቅረብ መብት ስለተሰጠን እናመስግን፤ ቁ. 14። ጸሎት እንዴት እንደሚሠራ ባናውቅም እንኳን፣ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘትና መነጋገርን ግን እናውቃለን። ጸሎት መብታችን ሲሆን፣ መብታችን ደግሞ ድፍረትን ይሰጠናል። ያንን እናውቃለን። ለንስሐ ድፍረት አለን፤ ለምስጋና ድፍረት አለን፣ ለልመና ድፍረት አለን፣ ለምልጃ ድፍረት አለን፣ ለአምልኮ ድፍረት አለን፣ ጸሎት መልስ አለው። መልሱ አዎን ወይም አይደለም ሊሆን ይችላል።

2. ጸሎት ሁኔታ አለው። በፊቱ መውደቅ፣ ዝቅ ማለት፣ መንበርከክ። ማናቸውንም ነገር እንደ ፈቃዱ ብንለምን ይሰማናል። በጸሎት አሳባችንንና ፍላጐታችንን በንግግራችን እየገለጽን እንድንጠይቅ ተነግሮናል።

እግዚአብሔር ፍላጐታችንን ያውቃል ብለን እንድንተው አልታዘዝንም:: እርሱ ሳይመልስልን በፊት መጠየቅ አለብን:: እኛ ስለጠየቅነው ሲል ብቻ የጸሎት መልስ ለመመለስ ተስፋ ባይሰጠንም እንኳን፣ እንደ ፈቃዱ እንደ ተስፋ ቃሉ መሠረት ይሰጠናል:: እንደ ቃሉ በእምነት ከኖርን ፍላጐታችንን እንደ ፈቃዱ ይፈጽምልናል፣ ማቴ. 21:22::

3. ጸሎት ፍጻሜ አለው:: ጸሎት የልባችንን አሳብና ምኞች መልስ ያመጣል:: ጸሎት የብረት መዝጊያን ይከፍታል:: ጸሎት ፊት ለፊት ያገናኛል:: ጸሎት ኀዘንን ወደ ደስታ ይለውጣል:: ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ያገናኛል:: ጸሎት ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር ያገናኛል::

3ኛ/ <u>ከኃጢአት የመከላከል ዋስትና ነው</u>፣ ቁ. 16-17 አንብብ::

ለዓለማችን የምንነግረው ሌላ ነገር፣ ኃጢአት መጥፎ እንደሆነ ነው:: ለሞት የማያደርስ ኃጢአት ወይም ሞት የማይገባው ኃጢአት አለ:: ለሞት የማያደርሰው ኃጢአት ያለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምን ክርስቲያን ነው:: በጌታ አምኖ በኃጢአት ለወደቀ ክርስቲያን ወንድም ወይም እኅት ምንም ዓይነት ኃጢአት እንኳን ቢሆን እንድንጸልይለት አስፈላጊ ነው:: በኃጢአት ለወደቁ ክርስቲያኖች የምናደርጋቸው ሁለት ነገሮች አሉ::

<u>የመጀመሪያው መንገድ</u>፣ በቀጥታ ለዚያ ወንድም መጸለይ ነው:: ስለ እርሱ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርና ለእርሱ መግለጽ ሲሆን፣

<u>ሁለተኛው መንገድ</u>፣ቀጥታ በኃጢአት ከወደቀው ክርስቲያን ወንድም ጋር መነጋገርና ነገሩን ማቃናት፣ ገላ. 6:1::

ጸሎት፣ በኃጢአት ለወደቀው ወንድምና እኅት መጸለይ ጌታ በንስሐ እንዲመለስ ያደርገዋል:: ጌታ ወደ ምሕረቱ ይመልሰዋል:: ሞት ለሚገባው የክርስቲያን ወንድም የኃጢአት ዋጋ ጌታ ዕዳውን ከፍሎለታል:: በንስሐ ሊመለስ ይችላልና እንጸልይ::

## ለሞት የሚያደርስ ኃጢአት

ለሞት የሚያደርስ ኃጢአት ወይም ሞት የሚገባው ኃጢአት ከተባለው ኃጢአት ሊያድን የሚችለውን ኢየሱስን መጥላት ነው:: ከኃጢአት ሊያነፃ ከሚችለው ከክርስቶስ ደም ጋር ፊት ለፊት መገናኘት አለፈልግም ማለት ለሞት የሚያደርስ ኃጢአት ነው፣ ዕብ. 10:26-29::

ሰው ክርስቶስን ከጠላ ሕይወትን ጠላ ማለት ነው:: ለእንደዚህ ዓይነት ሰው መጸለይ እንኳን ከባድ ነው:: ጸሎት ቢደረግም እንኳን ወደ እውነተኛ ጌታ ካልመጣ አይጠቅምም:: እንግዲህ ክርስቲያኖች ተስፋ በመቍረጥ መጸለይ እንዳንተው ጌታ ይርዳን፤1ኛ ሳሙ.12:23::

4ኛ ክርስቶስ በመካከላችን የመገኘት ዋስትና ሰጥቶናል፣ ቁ.18-21 አንብብ

ሐዋርያው ዮሐንስ ለተጠራጣሪ ዓለማችን በቁ. 19 ላይ ክፉ ዓለማችን ሲል፣ በዚያን ዘመን እንኳን ዓለም ክፉ መሆኑን ያረጋግጥልናል:: ይሁን እንጂ ሐዋርያው ዮሐንስ በዚያ ዘመን ዓለም ክፉ ቢሆንም እንኳ ብቻውን አልነበረም:: ከእርሱ ጋር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለነበረ ዋስትና ነበረው፣ ድፍረት ነበረው፣ ድል ነበረው:: ዛሬም ይህ ሁሉ ለክርስቲያኖች አላቸው:: ለክርስቲያን የሚያስፈልጉ በረከቶች ለሚመጣው ዓለም ብቻ ሳይሆን፣ በአሁኑ ዓለም፣ በአሁኑ ሕይወታችንም ዘመን እናገኘዋለን፤ ኢሳ.1:19:: ይህም እንዲሆን እናውቃለን እያለ 3 ነገሮችን ያስቀምጣል::

1. ለክርስቲያን አዲስ ኃይልና ችሎታ እንዳለው፣ ቁ. 18 አንብብ

ይህ አዲስ ኃይልና ችሎታ በክፉ መናፍስትና በሞራል ኃጢአት ላይ ነው:: ክርስቲያን እስካሁንም ድረስ ብዙ ፈተና ገጥሞታል:: ይሁን እንጂ በውስጡ ያለው አዲስ ሕይወት ድልን ይሰጠዋል:: የማያምን ሕይወት ሁሉ ኃጢአትን የሚሸከም ዕቃ ነበረ:: አሁን ግን በክርስቶስ በማመን ከእግዚአብሔር የተወለደ ስለሆነ ኃጢአትን አያደርግም:: ይህ

ቅዱስ መሆን ማለት ነው:: መቀደስ ማለት ለጌታ መለየት ማለት ነው:: ያለ ኃጢአት መሆን ማለት ነው::

እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ ይላል፣ 1ኛ ጴጥ. 1:15-16:: ፍጹም ቅዱስ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: እኛ እንደ እርሱ ፍጹም መሆን አንችልም:: ይሁን እንጂ የኃጢአት ልምምዶችንና በኃጢአት መመላለስን እንተዋለን:: በአዲስ መንገድም መጓዝ እንጀምራለን:: ከጌታ የተወለደ ክርስቲያን ሆነን ኃጢአትን መጥላት እንጀምራለን፣ ቁ.18 አንብብ:: ክርስቲያን ከኃጢአት ጋር ወዳጅነት ወይም ጓደኝነት የለውም:: በክርስቶስ አዲስ የተወለደ ሰው ራሱን ከኃጢአት የመጠበቅ ችሎታ ይሰጠዋል::

2. <u>ለክርስቲያን አዲስ መታወቂያ አለው</u>፣ ቁ.19 አንብብ

የክርስቲያኖች መታወቂያ ከዓለም መለየት ነው:: ከዓለም ወገን ስላይደሉ ከክፉ መለየት አለባቸው:: ነገር ግን ከክፉ የሚለዩት ጥቂቶች ብቻ ናቸው:: እነርሱ ለዓለም ሁሉ እንደ ጨው ናቸው:: ወይም እንደ ብርሃን እንደሆኑ ክርስቶስ ተናግሮአል፤ ማቴ. 5:13-14:: እነርሱ በዓለም ዘንድ የተናቁና ምናምንቴ ሲሆኑ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን የከበሩ ናቸው፤ 1ኛ ቆሮ. 1:27-30:: በክፉ ዓለም ውስጥ ሲኖሩ የቅዱሳንን ኑሮ ሊኖሩ ይችላሉ:: ይህ ነው መታወቂያቸው:: አንተስ ይህን መታወቂያ ይዘሃልን?

3. <u>ለክርስቲያን አዲስ እውቀት አለው</u>፤ ቁ. 20 አንብብ

በሰው ሕይወት ውስጥ ከሁሉ ነገር በላይ የሆነው ነገር እግዚአብሔርን ማወቅ ነው፤ ምሳሌ 9:10:: እግዚአብሔርን ማወቅ በእውነተኛ ክርስቲያን ልብ ውስጥ ብቻ ይገኛል:: ክርስቶስን በሚያምኑ ክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ ሁለት ዓይነት እውቀቶች አሉ::

<u>አንደኛው ዓይነት እውቀት</u> ባለፈው ዘመን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ፣ ሰው ሆኖ ወደ ምድር መምጣቱን ማወቅ ነው::

ሁለተኛው ዓይነት እውቀት በአሁኑ ዘመን የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በእምነትና በአዲስ ልደት ዛሬም ወደ ሕይወታችን መምጣት እንደሚችል ማወቅና በክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወቱን መሙላት ነው:: እርሱ ሕይወታችንን ሊለውጥ ይችላል::

ወዳጆቼ ሆይ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው:: ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ለእኛ መሞቱን፣ ዛሬም በሕይወታችን ውስጥ ገብቶ አዲስ ሊያደርገን እንደሚፈልግ ማወቅና ሕይወታችንን ለእርሱ መስጠት ከሁሉ የሚበልጥ እውቀት ነው፣ ዮሐ. 17:7-8::

እንደዚህ ዓይነት እውቀት ከወላጆቻችን የምንወርሰው ዓይነት ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው:: ይህ እውቀት በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ወደ እኛ ስለመጣ የዘላለም ሕይወት አለን ማለት ነው፤ 1ኛ ዮሐ. 5:13::

ይህንን አለማወቅ ግን ወደ መጨረሻው ወደ ዘላለም ሞት፣ ወደ ዘላለም ፍርድ፣ ወደ ዘላለማዊ የእሳት ባሕር ወይም ገሃነመ እሳት ያደርሳልና ከዲያብሎስና ከተከታዮቹ ጋር ወደ ዘላለም ሥቃይ የሚያደርስና ከእግዚአብሔር የሚለይ መሆኑን እወቅ፤ ማቴ. 25:41፤ ማር. 9:42-48፤ ራእይ 20:7-15፤ ምዕ. 21:8፤ ዮሐ. 5:29፤ ዳን. 12:2፣ ዕብ. 10:27:: ከዚያ የሚያድን ምንም የለም::

አንባቢ ሆይ፣ አንተስ በክርስቶስ የሚገኘው ሕይወት አለህ? ከሌለህ አሁኑኑ ጌታ ሆይ፣ ወደ እኔ ና ብለህ ጸልይና ተቀበለው::

## 4. ክርስቲያን ራስን የመጠበቅ እውቀት አለው፣ ቁ. 21

በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ክርስቲያን ራሱን የመጠበቅ እውቀት አለው:: ያውም ከኃጢአትና ከጣዖት መጠበቅ ነው:: ጣዖት ማለትም ማናቸውንም ነገሮች በሕይወታችን ከእግዚአብሔር በላይ ወይም እንደ እግዚአብሔር አድርገን የምንወድና የምናመልክ ከሆነ ያ ነገር ጣዖት ነው:: ለምሳሌ:-

1. በክርስቶስ አምኖ እግዚአብሔርን አለማወቅ ጣዖት ነው::
2. ለክርስቶስ ወንጌል ሳንታዘዝ ለራሳችን ፈቃድ መኖር ጣዖት ነው፤
3. ቤተሰብንና ወዳጅን ፈርቶ በጌታ አለማመን ጣዖት ነው፣ ማቴ. 10:37-38::
4. ገንዘብን መውደድ ጣዖት ነው፤1ኛ ጢሞ. 6:9-10::
5. በእውቀታችንና ችሎታችን መመካት ራሱ ጣዖት ነው፤ ኤር. 9:23-24 ተመልከት::

ዋናው ነገር በክርስቶስና በክርስቲያን መካከል የሚገባ ማናቸውም ነገር ጣዖት ነው:: ስለዚህ በጌታ ያለንን እምነት በጌታ ውስጥ ብንጠብቀው እምነትም እኛን ይጠብቀናል:: እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው:: ልጆች ሆይ፣ ከጣዖት ራሳችሁን ጠብቁ:: የመጠበቅ ኀላፊነት ተሰጥቶናልና:: አሜን::

እንግዲህ ክርስቲያን ወንድሜ ሆይ፣ ራስህን ከጣዖት ጠብቅ:: ራስህን ከኃጢአት ጠብቅ:: የመጠበቅ ኀላፊነት ተሰጥቶናልና:: ይህን ለማድረግ እግዚአብሔር ይርዳን አሜን::